# የኦሮሚኛ አፊ-ፈት ተማሪዎች ለንባብ ትምህርት ያላቸዉ ተነሳሽነት ከዉጤታቸዉ ጋር ያለዉ ተዛምዶ (በጅዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)


በ

ፍሬህይወት ቢረጋ


አማርኛን በማስተማር ዘዴ የማስተርስ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ
ጥናት


ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር



ነሐሴ፣ 2016ዓ.ም

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

# የኦሮሚኛ አፌ-ፈት ተማሪዎች ለንባብ ትምህርት ያላቸዉ ተነሳሽነት ከዉጤታቸዉ ጋር ያለዉ ተዛምዶ (በጅዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በጅማ ዩኒቨርሲቲ በማህበራዊ ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ እና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ

ፍሬህይወት ቢረጋ

የጥናቱ አማካሪ

ምህረት ሳዳሞ (ዶ/ር)

ነሐሴ፣2016 ዓ.ም

ጅማ፣ ኢትዮጵያ

**ጅማ ዩኒቨርሰቲ**

**የሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲ ኮሌጅ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋ (ዎች)ና ስነ-ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል**

**በማህበራዊ ሳይንስ እና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋ (ዎች) እና ስነ-ፅሁፍ ( አማርኛ) ትምህርት ክፍል**

**የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር**

በጅማ ዞን በአጋሮ ወረዳ በጅዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለንባብ ክህል ትምህርት ያላቸው ተነሳሽነትና የውጤት ተዛምዶ በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያነት በፍሬህይወት ቢረጋ የቀረበው ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል።

## የፈተና ቦርድ አባላት፤

ዋና አማካሪ ..........................................ፊርማ...............................ቀን...................

ረዳት አማካሪ………………………………ፊርማ……………………ቀን……………..

የውጭ ፈታኝ .............................................ፊርማ.........................ቀን.......................

የውስጥ ፈታኝ ............................................ፊርማ.........................ቀን........................

# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ ሁሉንም አሻግሮ ከዚህ ላደረሰኝ ልዑል እግዚአብሔር የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ ቀጥሎ ጥናቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ በረቂቁ እርማትም ሆነ በማስተካከያ አሰጣጥ ጠቃሚ ምክሮችንና ገንቢ አስተያየቶችን በመስጠት የዳበረ ሙያዊ ድጋፋቸው ያልተለየኝ አማካሪዎቼን ምህረት ሳዳሞ (ዶ/ር)ናማንያለው አባተ(ዶ/ር)ከልቤ አመስግናለሁ፡፡
በመረጃ አሰባሰብ ሂደት ጥናቱ በተካሄደበት በጅዳ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የጥናቱን ዓላማ ከተጠኚ ተማሪዎች በማስተዋወቅና መረጃ በማስሞላት አስፈላጊውን ትብብር ሁሉ ላደረጉልኝ መምህርት አዛለች አጥላው፣ መምህርት አለምፀሀይ ተሾመ፣ መምህር ታሪኩ ገሊሶ ከዚያም የተሰበሰበውን መረጃ በኮምፒውተር (ኮድ ሽት) በመጫን በ (SPSS) ስራ ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው አስፈላጊውን እገዛ ያደረጉልኝን መምህር ካሳሁን አዱኛ መረጃ በማቀበል የተባበሩኝን የወረዳውን አስተዳደር ጽ/ቤት፣ ትምህርት ጽ/ቤትና የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎችን በጣም ላመሰግን እወዳለሁ፡፡
የመማር ፍላጎቴን ተረድቶ የዩኒቨርሲቲ ትምህርቴን ስማር በፋይናንስና በሞራል ድጋፉ ያልተለየኝ ውዱ ባለቤቴ ገመቹ ሶሪ በሀሳብና በፀሎት ከእኔ ጋር ለነበሩት ውዷ እናቴ ወ/ሮአለሜ መስቀሌ እንዲሁም ልጆቼ ብሩክታዊት ገመቹ ፣ሮቤራ ገመቹ ፣ሄኖክ ገመቹ ከፍ ያለ ምስጋናን አቀርባለሁ፡፡

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**

ምስጋና.......................................................................................................................i
አጠቃሎ ........................................................................................... Error! Bookmark not defined.
ማውጫ......................................................................................................................ii
የሰንጠረዥ ማውጫ ..........................................................................................................iv
ምዕራፍ አንድ..............................................................................................................1
መግቢያ.......................................................................................................................2
1.1. የጥናቱ ዳራ .............................................................................................................2
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ...............................................................................................6
1.3. የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች.................................................................................................9
1.4. የጥናቱ ዓላማ .........................................................................................................10
1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ......................................................................................................10
1.6. የጥናቱ ወሰን .........................................................................................................11
1.7. የቁልፍ ጽንሰ ሀሳቦች አጠቃቀም ብያኔ ...........................................................................12
ምዕራፍ ሁለት ...........................................................................................................13
ክለሳ ድርሳናት.............................................................................................................13
2.1. ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝት ....................................................................................................13
2.1.1 የንባብ ምንነት .........................................................................................................13
2.1.2.. የንባብ ትምህርት ዓላማ..............................................................................................13
2.1.3. አንብቦ የመረዳት ምንነት ............................................................................................14
2.1.4. በአንብቦ መረዳት ተግባራት የክፍል ውስጥ ትግበራ ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎች ..........................15
2.1.4.1 የተማሪዎች ተነሳሽነት..................................................................................................15
2.1.4.2 በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ብዛት ..................................................................15
2.1.4.3.የተማሪዎች ቅድመ እውቀት እና የቋንቋ ችሎታ መለየት.........................................................15
2.1.4.4 አቀላጥፎ አለማንበብ...................................................................................................15
2.1.5 የተነሳሽነት ምንነት......................................................................................................16
2.1.6 የተነሳሽነት ዓይነቶች....................................................................................................17
2.1.7 ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት አይነቶች....................................................................................18
2.1.8. ተነሳሽነት ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤትጋር ያለው ተዛምዶ ................................................20
2.1.8.1. ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት............................................................................................20

2.1.8.2. ውህዳዊ ና ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት 20
2.1.8.3. ውስጣዊና ውጫዊ ተነሳሽነት 21
2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት 22
ምዕራፍ ሦስት 26
የጥናቱ ዘዴና አካሄድ 26
3.1. የጥናቱ ዘዴ 26
3.1.1.የጥናቱ አካላይ 26
3.1.2. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ 26
3.1.3. የተጠኚ ተማሪዎች አመራረጥ 27
3.2. የመረጃ መሰብሰቢያዎች 28
3.2.1. የጽሑፍ መጠይቅ 28
3.2.2. የችሎታ መለኪያ ፈተና (Achievement Test) 30
3.2.3.ምልከታ 31
3.3. የመረጃ አተናተን ዘዴ 32
ምዕራፍ አራት 33
4. የመረጃ ትንተናና ማብራሪያ 33
4.1 የመረጃ ትንተና 33
4.1.1. የጥናቱ ተሳታፊዎች አጠቃላይ መረጃ 33
4.1.2. የፈተና ውጤት 33
4.1.3. የተማሪዎችን የንባብ ተነሳሽነት የሚያሳይ ገላጭ እስታትስትክስ 34
4.1.4. የተማሪዎች የንባብ ተነሳሽነት እና የውጤት ተዛምዶ 35
4.1.5 ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ 36
4.1.5.1 ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና 37
4.2. የውጤት ማብራሪያ 38
ምዕራፍ አምስት 40
5. ማጠቃለያ መደምደሚያ እና መፍትሔ 40
5.1 ማጠቃለያ 40
5.2 መደምደሚያ 41
5.3 የመፍትሔ ሃሳብ 42
ዋቢ መጻሕፍት 43
አባሪ ሀ የጽሁፍ መጠይቅ 45
አባሪ ለ ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ 49
አባሪ ሐ: የአማርኛ ፈተና 50
አባሪ መAPPENDIX –ENGLISH VERSION 55

## ሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ ሀ ከተነሳሽነት አንጻር ባህሪያዉያን፤ አእምሮታዊያን እና ግንባታዉያን ያላቸዉ እይታ። ......16
ሰንጠረዥ ለ የውስጣዊና የውጫዊ ተነሳሽነት ንጽጽር ......21
ሰንጠረዥ ሐ:የጥናቱ ተሳታፊዎች አጠቃላይ መረጃ ......33
ሰንጠረዥ መየፈተና ውጤት ......33
ሰንጠረዥ ሠ የተማሪዎችን የንባብ ተነሳሽነት የሚያሳይ ገላጭ እስታትስትክስ ......34
ሰንጠረዥ ረየተማሪዎች የንባብ ተነሳሽነት እና የውጤት ተዛምዶ ......35
ሰንጠረዥ ሰ ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ......36

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት የአፋን ኦሮሞ አፍ-ፈት ተማሪዎች ለንባብ ትምህርት ያላቸውን ተነሳሽነትና የውጤት ተዛምዶ መፈተሽ ነው፡፡ ጥናቱ የተካሄደው በጅማ ዞን በአጋሮ ወረዳ በጅዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2016 ዓ.ም በመማር ላይ በሚገኙ 110 የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ነው፡፡ በዕጣ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ከተመረጡት ተማሪዎች በጽሑፍ መጠይቅ፣ በፈተና እና በምልከታ የጥናቱ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በገላጭ ስታቲሲቲክሶችም ተተንትኖ የተብራራ ሲሆን በመረጃው ትንተና መሠረት በተማሪዎቹ የንባብ ትምህርት የመማር ተነሳሽነትና በንባብ ትምህርት ውጤት መካካል የጎላ ተዛምዶ አልታየም፡፡ በተነሳሽነት አይነቶችና በንባብ ትምህርት ውጤት መካከልም ተዛምዶ አልታየም፡፡ ከጥናቱ ውጤት በመነሳት ሁለተኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን የንባብ ትምህርቱን ሲያቀርቡ የተማሪዎችን ፍላጎትና ስሜት በሚያነሳሳ መልኩ ቢያቀርቡ፣ ተማሪዎች ምን አይነት ማበረታቻ ቢደረግላቸው በንባብ ውጤታማ እንደሚሆኑ አስቀድሞ በማወቅ የተማሪዎችን የንባብ ተነሳሽነት ለማጠናከር የሚረዱ ተግባራትን ቢያከናውኑና ይህንኑ መሠረት ያደረገ ድጋፍና ክትትል ቢያደርጉ የተማሪዎቹ የንባብ ተነሳሽነት ሊሻሻል ይችላል የሚሉ የመፍትሔ ሀሳቦች ተጠቁመዋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

የማንበብ ክሂል ቋንቋን በማስተማር ሂደት ጉልህ ድርሻ አለው፡፡የዚህ ክሂል በአግባቡ መዳበር ለሌሎች ክሂሎች መዳበር ወይም ማደግ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡የተሻለና ጥሩ አንባቢ ለመሆን የዳበረ የንባብ ችሎታ እና የንባብ ተነሳሽነት ያለው መሆን ያስፈልጋል፡፡ የንባብ ችሎታ ሲባል በንባብ ሂደት የምንጠቀምባቸውን የተለያዩ የንባብ ስልቶች ፣የንባብ ተነሳሽነት እና የንባብ ፍጥነትን ያጠቃልላል፡፡

ንባብ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ንባብን ምሁራን በተለያየ መንገድ ገልፀውታል Nuttal (1982) ንባብ ማለት አላማ ያለው የሚፈለግን መረጃ ከፅሁፍ ውስጥ ማግኘት ነው፡፡ይህ ብያኔ የሚያመለክተው ንባብ በፅሁፍ የቀረበን መልእክት አጣጥሞ መገንዘብን የሚገልፅ መሆኑን ነው፡፡ንባብ ለአንድ አላማ የሚፈለግን መረጃ ወይም የፅሁፍ መልእክትን ለማግኘት ወይም ለማወቅ የሚደረግ አላማ ያለው ተግባር መሆኑን ነው፡፡

Brown (1994) እንደገለፁት ማንበብ በአብዛኛው ከትምህርት ቤት ውጭ የሚለመድ ክሂል አይደለም፡፡ ሰዎች ማንበብን የሚማሩት እና የሚያዳብሩት ወደ ትምህርት ቤት በመሄድ እና በመለማመድ ነው፡፡ ስለሆነም ቋንቋ በሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶች የማንበብ ትምህርት ሰፊ ቦታ የሚሰጠው ክህል መሆኑን Brown (1994) ሲገልፁ በተጨማሪም Patirica and Pamela (2004) በትምህርት ቤት ከሚቀርቡ የእውቀትና የክህል ዘርፎች የንባብ ትምህርት ትልቁንድርሻ እንዲይዝ መደረጉን ያብራረሉ፡፡

በማንበብ አእምሮው የዳበረ ትውልድ ራሱንእና በዙሪያው ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ በተሻለ ሁኔታ መገንዘብና መግለፅ እንደሚችል በርካታ ምሁራን የሚስማሙበት ጉዳይ ነው፡፡ Khairuddin (2013) ንባብ በዚህ የቴክኖሎጂ እድገት በፍጥነት እየተለወጠ እና ስልጣኔ ባለበት አለም ውስጥ የሰው ልጅ በመረጃ ላይ የተመሰረተ እውቀት እንዲኖረው በማድረግ ረገድ ጉልህ ድርሻ አለው፡፡

Grellet (1981) ንባብ ማለት መገመት መተንበይ ማመሳከር እራስን ጥያቄ መጠየቅ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ የሚፈልግ ሂደት ነው፡፡ በሂደቱም አንባብቢ ከምንባቡ አውድ በመነሳት የአዳድስ ቃላት ፍቺን የሚገመግምበት ገና ከመነሻው ባገኘው መረጃ ላይ በመመርኮዝ የምንባቡን ዋና ይዘትና ወደ ፊት ምን እንደሚገጥመው የሚተነብይበት ያነበበውን ፅሁፍ

መረዳት አለመረዳቱን እራሱን የሚጠይቅበት በመጠየቅ የሚያመሳክርበት ሂደት መሆኑን እንረዳለ፡፡

Girlet (1990) የንባብ ትምህርት አላማን ሲያብራሩ ንባብ የምናስተምረው ተማሪዎች አጠቃላይ እውቀታቸውን ለማሳደግ እንዲችሉ መሰረታዊ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማሳደግ የአጠቃላይ እውቀት ይዘት ያላቸውን ፅሁፎች ማንበብና መረዳት እንዲችሉ ማስቻል ነው፡፡ Girlet1981 አንብቦ መረዳት ማለት ከአንድ ፅሁፍ ውስጥ ተፈላጊ መረጃ በብቃት ማሰባሰብ መቻል ማለት ነው ይላሉ፡፡

Hugs (1989) ተማሪዎች አንድ ፅሁፍ የያዘውን ሀሳብ ተረድተዋል ለማለት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በሙሉ መመለስ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ነገርግን የሰው አእምሮ በፅሁፍ የቀረቡ ሀሳቦችን ከተለያዩ አቅጣጫዎች በመመልከት የሚገነዘብ በመሆኑ የአንብቦ መረዳት ተፈታኞች 80 ከመቶ በላይ ውጤት ካስመዘገቡ የቀረበውን ፅሁፍ ተረድተውታል ማለት እንደሚቻል ያስረዳሉ፡፡

Madsen (1983) ከበቂ ፍጥነት ጋር የተሰጣቸውን ፈተና 40 ከመቶ በታች ከሆነ በጣም ዝቅተኛ ከ50-41 በመቶ ዝቅተኛ ከ69-51 በመቶ መካከለኛ ከ70-80 በመቶ በቂ ከ81 በመቶ እና ከዚያ በላይ ከሆነ ደግሞ ከፍተኛ አንብቦ መረዳት ችሎታ አላቸው በማለት ማስቀመጥ ይቻላል ይላሉ፡፡

ተነሳሽነት ሰዎች አንድን ተግባር እንዲፈጽሙ የሚገፋፋ ውስጣዊ ስሜት ነው፡፡ Harmer ,(1991) ይህንኑ ፅንሰ ሀሳብ Brown (1987) ተነሳሽነት በሰው ልጆች ላይ የሚታይ ተፈጥሯዊ የሆነ አንድን ነገር ለመተግበር የሚያስችል ውስጣዊ ፍላጎት መሆኑን ያብራራሉ፡ ፡ይህም የሚያሳየን የንባብ ተነሳሽነት የተለያዩ ዓላማዎችን መሰረት በማድረግ አንድ የሚነበብ ነገር ለምንና እንዴት እንደሚነበብ የሚያሳይ የባህሪይ ተፅዕኖ ሊያመጣ የሚችል ግፊት መሆኑን ነው፡፡

ተነሳሽነትን ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት አኳያ ስንመለከተው እንደ ትምህርት ውጤት መግለጫ ሆኖም ያገለግላል Gardner (1985)፡፡ አክለውም Gardner ከዚህም በተጨማሪ ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት ከውጤት ጋር ብቻ ሳይሆን ከቋንቋ መማር ሂደት ጋርም ግልጽ የሆነ ግንኙነት እንዳለው ያስረዳሉ፡፡ እንደ Gardner አገላለጽ የንባብ ተነሳሽነት በጥረት የንባብ ዓላማን የማሳካት፣ ምኞትና ለማንበብ የሚያስችሉ የጥሩ አመለካከቶች ቅንጅት ነው፡፡ ይህም የሰዎችን ፍላጎት፣ ስሜት፣ ጉጉት የሚያንፀባርቅ ከውስጣዊ ወይም ከውጫዊ ግፊት በመነሳት ቀና አመለካከትን፣አዎንታዊ ምላሽን እና ጥሩ ውጤትን

የሚያስገኝ አንድ ንባብ እንዲነበብ የሚያበረታታ ሂደት መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከዚህ አንፃር የንባብ ተነሳሽነት ግለሰቡ ለማንበብ ካለው ምኞትና ከማንበብ ለሚያገኘው እርካታ ሲል የሚያከናዉነው ስራ ወይም የሚያደርገው ጥረት እንደሆነ ይስተዋላል፡፡

በመማር ማስተማሩ ሂደትም በተማሪዎች ላይ የባህርይ ለውጥ እንዲታይ ተነሳሽነት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል Bill (2000)፡፡ እንደ Bill አገላለጽ የንባብ ትምህርትን በተነሰሽነት የሚማር ተማሪ ባነበበው ንባብበ ዙሪያ ግንዛቤን፣ ትውስታንና አዕምሯዊ ዕድገትን ያገኛል፤ ምክንያቱም የንባብ ተነሳሽነት ያለው ተማሪ በንባብ ትምህርቱ ላይ አዎንታዊ አመለካከት ስለሚኖረው ለማንበብ ይደፋፈራል፤ አእምሯዊ፣ መንፈሳዊና አካላዊ ጥረት ያደርጋል፡፡ ከዚህም የተነሳ ካለመው ግብ ይደርሳል፡፡ በመሆኑም ከዚህ ድምዳሜ የንባብ ትምህርት ለመማር ተነሳሽነት እንደ አንድ መሳሪያ የሚቆጠር ለተማሪዎች አስፈላጊና መሰረታዊ ጉዳይ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

Brown (2000) ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነትን ውህዳዊና ጥቅማ ጥቅማዊ በማለት በሁለት ይከፍሉታል፡፡ ውህዳዊ ተነሳሽነት የሚባለው የታላሚው ቋንቋ ተማሪዎች ከቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ አባላት ጋር ውህደት ወይም ቅርበት ለመፍጠር ከማሰብ አኳያ ቋንቋውን ለመማር የሚነሳሱበት የተነሳሽነት ዓይነት ነው Elli (1995)፡፡ ይህም ተማሪዎች ለታላሚው ቋንቋ ተናጋሪዎች ቋንቋና ባህል፣ማህበራዊ አኗኗር፣መልካም አመላካከት ስለሚኖራቸው በቋንቋው የተፃፉ ፅሁፎችን ለማንበብ የሚኖራቸው ተነሳሽነት ጠንካራ ሊሆን እንደሚችል ያስረዳል፡፡

ሌላው የተነሳሽነት ዓይነት ከውህዳዊ ተነሳሽነት ጋር አብሮ የሚነሳው ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ነው፡፡ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ተጨባጭ ጥቅማ ጥቅም ለማግኘት ቋንቋውን የሚማሩበት የተነሳሽነት ዓይነት ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ይባላል Ellis (1997)፡፡ ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነትን Norris (2001) አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ የሚያነቡበት ዓላማ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም የዩኒቨርሲቲ መግቢያ መስፈርት ለማሟላት የተሻለ ደመወዝ ወይም ክፍያ ለማግኘት ዓለምአቀፋዊ መረጃና ዕውቀት ለማግኘት የሚሉት ዋና ዋና የጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ዓላማዎች መሆናቸውን ያስረዳሉ፡፡

ሌሎች በምሁራን ተደጋግመው የሚነሱት የቋንቋ መማር የተነሳሽነት ዓይነቶች ውስጣዊና ውጫዊ ተነሳሽነት የሚባሉት ናቸው Brown (2000)፡፡ ውስጣዊ ተነሳሽነት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ ከውስጥ በሚመነጭ ግፊት በማንበብ ተግባራትን በማከናወን

የሚገኝ የተነሰሸነት ዓይነት ሲሆን ተመሪዎቹ የመምህሩ የማስተማር ስልት ቢያረካቸውም ባያረካቸውም ትምህርቱ ፈተና ይኑረው አይኑረው ከማንበብ ወደ ኋላ የማይሉበት የተነሳሽነት ዓይነት ነው፡፡ የውስጣዊ መነሳሳት ባህሪያት ውስጣዊ ምላሽ የሚያስገኙ ውጤቶች ሲሆኑ እነዚህም የብቃት ስሜቶችና ግላዊ ውሳኔ ናቸው፡፡

ውጫዊ ተነሳሽነት ደግሞ ሌላኛው ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት ዓይነት ነው፡፡ ውጫዊ ተነሳሽነት በመምህራን፣በወላጆች እና በጓደኞች ወይም በሌላ አካል ለመወደስ፣ ለመሸለም’፣ ለመመስገን፣ በፈተና ጥሩ ውጤት ለማስመዝገብ እና ጥፋትን ቀንሶ ቅጣት ለማስቀረት የመሳሰሉ የአጭር ጊዜ ግቦችን የሚያስገኝ የተነሳሽነት ዓይነት ነው፡፡Stern፣ (1994) Noels (2003) Chtterrje (2000) አክለው ውጫዊ የመነሳሳት ባህርያት ከግለሰቡ ከራሱ ውጭ ከሆነ አካል ምላሽ ያስገኛሉ ተብለው የሚገመቱ ናቸው፡፡ ውጫዊ ምላሾች የሚባሉት ገንዘብ፣ ሽልማት፣ ማርክና አዎንታዊ ግብረ-መልሶች ናቸው፡፡ በመሆኑም ታላሚውን ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎችን ንባብን የመማር ተነሳሽነት ማጥናቱ በተለያዩ ተመራማሪዎች የተጠቀሱትንና ለስኬት መጥፋት መንስኤ የሚሆነውን ችግር በማቃለል የተማሪዎችን ስኬታማነት ወደፊት ያራምዳል፡፡የንባብ ተነሳሽነትና የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ተዛምዶን አስመልክቶ በተለምዶም ቢሆን ከተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ባህሪይ መረዳት እንደሚቻለው አንድ ተማሪ በቋንቋ ትምህርት ፈተናው ጥሩ ውጤት የሚያስመዘግበው ታላሚውን ቋንቋ የማንበብ ምኞት ሲኖረውና ተሽሎ ለመገኘት ጥረት ሲያደርግ ነው እንዲህ አይነቱ ተማሪ የአንብቦ መረዳት ችሎታም ይኖረዋል ተብሎይገመታል፡፡

በዓለም ላይ ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት ከትምህርት ውጤት ጋር የሚኖረውን ዝምድና ለመፈተሽ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ በመስኩ ቀዳሚነት እንዳላቸው የሚገመቱት Gardner and Lambert (1972) በአሜሪካዊያን ዐውድ ውስጥ ከእንግለዝኛ ወይም ከፈረንሳይኛ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ በመጡትና የፈረንሳይኛ ቋንቋን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ከሚማሩት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ናሙናዎችን ወስደው የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ተለዋዋጮችንና የትምህርት ውጤት ተዛምዶ በሚመለከት ምርምር አካሂደዋል በውጤቱም የቋንቋ ተሰጥኦ የተነሳሽነት መጠንና የፈረንሳይኛ ቋንቋን ለመማር ያለ ምኞትን በተመለከተ ከተጠኝዎች በተገኘው መረጃ የተጠቀሱት ተለዋዋጮች ከትምህርት ውጤት ጋር ያላቸው ተዛምዶ ዝቅተኛ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

በመሆኑ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ክህል ትምህርት ተነሳሽነትን ከውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ ማጥናት ስነ-ልቦናዊ ችግሮችን በማቃለል ውጤታማ የሚሆኑበትን ሁኔታ ከማመቻቸት አንፃር ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ተነሳሽነት አንድን ነገር ለመተግበር ወደ ውሳኔ የሚመራ የአእምሮና የስሜት መቀስቀስ ሁኔታን ዘላቂነት ወዳለው አዕምሯዊና አካላዊ ጥረት የሚያነሳሳ በቅድሚያ የታቀደ ግብን ለማሳካት የሚረዳ ነገር ነው፡፡ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ቋንቋውን የሚማሩት ከቋንቋው ተናጋሪዎች ባህል ጋር ትስስር ለመፍጠር ከሆነ ተነሳሽነታቸው ውህዳዊ ነው፤ ነገር ግን ሁለተኛ ቋንቋውን የሚማሩበት ምክንያት በቋንቋው ጥቅም ለማግኘት ከሆነ ደግሞ ተነሳሽነታቸው ጥቅማ ጥቅማዊ ነው፡፡ Gardner፣ (1972)፡፡ ሌላው ሰዎች የሚያከናውኑት ተግባር ስለ አንድ ጉዳይ ለማወቅ ለመረዳትና እርካታን ለማግኘት ከሆነ ተግባራቸው ውስጣዊ ተነሳሽነት መሰረት ያደረገ ሲሆን የሚያከናውኑት ተግባር ከተግባሩ ውጭ ከሆነ አካል ጋር ሆኖ አዎንታዊ ግብረ መልስ ለማግኘት ከሆነ ደግሞ ተግባራቸው በውጫዊ ተነሳሽነት ላይ የተመሰረተ ነው Nakamura፣ (1989)፡፡

በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ክንውን ተማሪዎችን በቋንቋ ትምህርቱ ውጤታማ ከሚያደርጉት ምክንያቶች አንዱ ተነሳሽነት ነው Littlewood፣ (1981)፡፡ እንደገለጹት ማንበብን በቀዳሚነት የመቀስቀስ በማንበብም ያገኙት ዕውቀት ዘለቄታ እንዲኖረው የመርዳት በአጠቃላይ ለንባብ ትጉህ የማድረግ ተግባር የተነሳሽነት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ከተነሳሽነት ውጭ ግብ መቼና አጥጋቢ ውጤት ተግባራዊ ሊሆን አይችልም ይላሉ፡፡

ከአስተያየቱ ለመረዳት እንደሚቻለው የንባብ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች በንባብ ትምህርት ሂደት ውስጥ ተሳታፊነት እንዳላቸው ከተግባራቱም ተጠቃሚ ለመሆን ተነሳሽነቱ የተሻለ ዕድል እንደሚፈጥርላቸው በተቃራኒው ደግሞ የንባብ ተነሳሽነት የሌላቸው ተማሪዎች በተግባራቱ በብቃት እንደማይሳተፉና በንባብ ትምህርታቸው ደካማ እንዲሆኑ እንደሚያደርጋቸው ይስተዋላል፡፡

Gardiner (1985) ተነሳሽነት በአመለካከቶችና በትምህርት ውጤት መካከል ያለውን ተዛምዶ የሚያመቻች ነው፡፡ የሚለውን መላምት ለማረጋገጥ ከሁለት አካባቢዎች መረጃ ሰብስበው ባካሄዱት ጥናት የተነሳሽነት ተጽእኖዎች ወይም አላባውያን በጥናቱ በማይካተቱበት ጊዜ በአመለካከት ልኬታዎችና በትምህርት ውጤት መካከል የሚኖረው የተዛምዶ መጠን እንደሚቀንስ ወይም ጉልህነት እንደሌለው በተጨማሪም የአመለካከቶች ልኬታዎች

ባልተካተቱበት ሁኔታ በተነሳሽነትና በቋንቋ ትምህርት ውጤት መካከል የሚኖረው ተዛምዶ ተጽእኖ ሊደርስበት የማይችል ስለ መሆኑ ተብራርቷል።በሌላ መልኩ ደግሞ በመስኩ ከተካሄዱት የምርምር ስራዎች መካከል እያንዳንዱ የተነሳሽነት ዓይነት ከትምህርት ውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ ካመላከቱት የምርምር ውጤቶች በ Brannon (2000)። የተጠቀሰው በ Gardner & Lambert (1972)። በበፊሊፒንስ የተካሄደ ጥናት ነው። በምርምሩ Gardner & Lambert የፊሊፒንስ ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃታቸውን ለማሳደግ ሲያሳዩ የነበረው ጥረት ከእንግሊዝኛ ተናጋሪ ማህበረሰብ ጋር ውህደት ለመፍጠር ሳይሆን በቋንቋው ጥቅማጥቅም ለማግኘት እንደነበር Brown (2000) ያስረዳሉ።

በመሆኑም Gardner እና Lambert ከፊልፒንሱ የጥናት ግኝታቸው በመነሳት በጥቅማጥቅማዊ ተነሳሽነት ሁለተኛ ቋንቋን ውጤታማ በሆነ መንገድ መማር እንደሚቻል አረጋግጠዋል Brown፣ (2000)።

Ellis (1995) & Freeman & Long (1992) ዋቢ ያደረጓቸው Barstol፣ (1975)። በሁለተኛ ቋንቋነት የፈረንሳይኛ ቋንቋን በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ባካሄዱት ምርምር ላይ በተናጠል ሳይሆን በአንድነት ውህዳዊና ጥቅማጥቅማዊ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች በፈረንሳይኛ ቋንቋ ትምህርታቸው ውጤታማ እንደሆኑ ይገልጻሉ።በጥናቱ ውጤት መሠረት ተማሪዎቹ ከትምህርት ቤት ውጪ ለፈረንሳዊያንና ለባህላቸው በትምህርት ቤት ውስጥ ደግሞ ለፈረንሳይኛ ቋንቋ መልካም አመለካከት አሳይተዋል።

በሌላ በኩል Noel፣ (2001)። ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነትን የበለጠ ለማሳደግ ውስጣዊ ተነሳሽነት ትኩረት እያገኘ መምጣቱን Dorneeign፣ (1998,1990)። Brown፣ (1990)። እና ሌሎች በርካታ ተጨባጭ ምርምር ያካሄዱ ተመራማሪዎችን በመጥቀስ ከውጫዊ ተነሳሽነት የበለጠ ውስጣዊ ተነሳሽነት ብልጫ እንዳገኘ አመላክተዋል። Noels ውስጣዊ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች የጭንቀት መጠናቸው ዝቅተኛ ይሆናል። ስለሚማሩት ቋንቋ አዎንታዊ አመለካከት ይኖራቸዋል። ቋንቋ የመማር ብቃታቸውም ይጨምራል በማለት ያብራራሉ።በተመሳሳይ ሁኔታ Harmer ፣ (2001) & Ellis ፣ (1997)። ውስጣዊ ተነሳሽነት ከሌሎች የተነሳሽነት አይነቶች ይልቅ በሁለተኛ ቋንቋ ውጤታማ ያደርጋል በሚል ሀሳቡን ያጠናክራሉ።

Pintritch፣ & Schunk፣ (2000) & Gardner፣ (1994)።ውጫዊ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች ቁሳዊ ሽልማትን ተስፋ በማድረግ የሚፈጠር ተነሳሽነት በመሆኑ ሽልማቱ ሲቋረጥ የተማሪዎቹን የመማር ተነሳሽነት ይቀንሰዋል በሚል የዚህን አይነት ማበረታቻን

ይቃወማሉ፡፡ ማበረታቻን ተስፋ ከማድረግ ይልቅ ተማሪዎቹ በራሳቸው ተነሳሽነት ቢማሩ ውጤታማ እንደሚሆኑ በመግለጽ የውስጣዊ ተነሳሽነትን ጠንካራ ጎን አጉልተው ያብራራሉ፡፡

በሀገራችንም የአማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ ተማሪዎች ላይ በክፍሌ (2002) እና በዓለምነሽ (2001) በተጠኑት ምርምሮች በውስጣዊ ተነሳሽነትና በትምህርት ውጤት መካከል ጉልህ ተዛምዶ መኖሩ ተመልክቷል፡፡ ውጫዊ ተነሳሽነትግን በሁለቱም ጥናቶች የትምህርቱ ውጤት ተንባይ ሆነው አልተገኙም፡፡ በሌላ በኩል Noels፣ (2001) ውስጣዊም ሆነ ውህዳዊ የመማር ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች ለሚማሯቸው የትምህርት ተግባራትና ለመማር ሂደቱ አዎንታዊ አመለካከት ስለሚኖራቸው ሁለቱ የተነሳሽነት አይነቶች ተመሳሳይነት እንዳላቸው ይስማማሉ፡፡

ስመኝ (2002) ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ላይ ያላቸው ተነሳሽነት በሁሩሙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 9ኛ ክፍል ተተኳሪነት በሚል ርእስ ያጠናችው ጥናት ሲሆን ያገኘችው ውጤት የተማሪዎቹ ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆኑን ገልፃ ፡፡ዝቅተኛ ለመሆኑ ምክንያት ስታስቀምጥ የመማሪያ መፅሀፍ እጥረት መፅሀፉ የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ያለማገናዘቡ እንዲሁም በተማሪዎች ተነሳሽነት ላይ የመምህራን ተሳትፎ የቀዘቀዘ መሆኑን በመግለፅ ለወደፊት ለተማሪዎች ተነሳሽነት ላይ ትኩረት እንድሚገባ ጠቅሳለች፡፡

ዮሀንስ ሰለሞን (2013) የአንብቦ መረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ ትንተና ጉጂ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 10ኛ ክፍል ተተኳሪነት በሚል ርእስ ያጠናው ጥናት ሲሆን ያገኘው ውጤት የተማሪዎቹ አንብቦ መረዳት ችሎታ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ እንደሆነእና የንባብ ፍጥነታቸውም ዝቅተኛ በሚባል ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አሳውቋል፡፡ በዚህ መሰረት የአንብቦ መረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት መካከለኛ ተዛምዶ እንዳለው አመላክቷል፡፡

ተስፋዬ ኦላና (2014) ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያለቸው ተነሳሽነት እና የውጤት ተዛምዶ በሁሩሙ እና በሶንጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ10ኛ ክፍል ተተኳሪነት በሚል ርእስ ያጠናው ጥናት ሲሆን ያገኘው ውጤት የተማሪዎቹ ተነሳሽነት መካከለኛ መሆኑ እና ውጤታቸው ዝቅተኛ መሆኑን ገልጿል ምክንያቱን ሲያስቀምጥ የመማር ማስተማሩ ሂደት ከተማሪዎቹ የመማር ተነሳሽነት ጋር የማይጣጣም ሊሆን ይችላል ብሏል፡፡

በአጠቃላይ ተነሳሽነትን አስመልክቶ በሁለተኛ ቋንቋ መማርና በትምህርቱ ውጤታማ በመሆንና ባለመሆን ዙሪያ የጠበቀ ግንኙነት መኖሩን ከላይ ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡ ይሁን

እንጂ ተማሪዎች የትኛውም የተነሳሽነት አይነት ሊኖራቸወ ይችላል፤ ሆኖም ግን ንባብን በተሳካ ሁኔታ የሚያነቡበትን እና አንብበው የሚረዱበትን የተነሳሽነት አይነት በመለየት የትምህርት ውጤታቸውንየሚያሻሽሉበት፣እንዲሁም የንባብ ችሎታቸውን የሚያጎለብቱበትን ሁኔታ ለመፍጠር ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል። ምክንያቱም በጥናት ላይ የተደገፈ የመማር ማስተማር ተግባር የተሳሳተውን አቃንቶ ጠንካራውን አበርትቶ ለአስተማማኝ ውጤት ያበቃልና።

በመስኩ በየጊዜው በተለያዩ ተመራማሪዎች በተለያዩ ቦታዎች ጥናቶች ይካሄዳሉ። ከዚህም በመነሳት ለንባብ ትምህርት የመማር ማስተማር ስኬታማነት እና የተሻለ ዉጤት መገኘት አሁንም ስለንባብ ተነሳሽነትና የውጤት ተዛምዶ ማጥናት አስፈላጊ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ይህ ደግሞ ለዚህ ጥናት መካሄድ መነሻ ምክንያት ቀዳሚ ጉዳይ ሆኗል። ተከታዩ ምክንያት አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩት የአፋን ኦሮሞ አፍ-ፈት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ለንባብ ትምህርት ያላቸው ተነሳሽነትና የውጤት ተዛምዶን በሚመለከት ከታዩት የመረጃ ምንጮች ቀደም ሲል የተካሄደጥናት በትምህርት ቤቱ ባለመገኘቱ ሲሆን ሶስተኛው ምክንያት አጥኝዋ በትምህርት ቤቱ ባደረገችው ቅኝት የአብዛኞቹ የአፋን ኦሮሞ አፍ-ፈት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት በተደጋጋሚ አጥጋቢ አለመሆኑን በማስተዋሏ ነው። ከዚህ የተነሳ የተማሪዎቹ ውጤት ተማሪዎቹ ለንባብ ክሂል ትምህርት ካላቸው ተነሳሽነት ጋር ምን ያህል ተዛምዶ አለው? የሚል ጥያቄ በአጥኚዋ አእምሮ ተጭሯል። በዚህ ምክንያት ተጨማሪ ጥናት እንደሚያስፈልግ ተገንዝባለች። ጥናቱም ለሚከተሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል ተብሎ ይገመታል።

## 1.3. የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

ሀ. ተማሪዎቹ ለንባብ ክሂል ያላቸው ተነሳሽነት ምን ያህል ነዉ?

ለ. በየትኛው የተነሳሽነት አይነት ነው የተሻለ መነሳሳት ያላቸው?

ሐ.ተማሪዎቹ ለንባብ ክሂል ትምህርት ያላቸው ተነሳሽነት ከአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤታቸው ጋር ያለው ዝምድና ምን ያህል ነው?

## 1.4. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋነኛ አላማ በጅማ ዞን በአጋሮ ወረዳ በጅዳ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ክሂል የመማር ተነሳሽነት ከትምህርት ውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ መመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረት የሚከተሉት ንዑሳን አላማዎች ይኖሩታል፡፡

ንዑሳን አላማዎች፡-

ሀ. ተማሪዎቹ ለንባብ ክሂል ትምህርት ያላቸው ተነሳሽነት መፈተሽ

ለ. ተማሪዎቹ የበጠ መነሳሳት ያሳዩበትን የተነሳሽነት አይነት መፈተሽ

ሐ. ተማሪዎቹ ለንባብ ክሂል ትምህርት ያላቸው ተነሳሽነት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤታቸው ጋር ያለውን ዝምድና  መፈተሽ

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ሊኖሩት ይችላል፡፡

ሀ. ተማሪዎቹ በጥናቱ ውጤት ላይ ተመርኩዘው በንባብ ትምህርት ውጤታማ ሊያደርግ የሚችል የተነሳሽነት ዓይነት  መስመር ለመያዝ ጥረት እንዲያደርጉ ሊያነሳሳ ይችላል፡፡

ለ. በንባብ ትምህርት መማር ላይ አነስተኛ ተነሳሽነት ላላቸው ተማሪዎች አስፈላጊና ጠቃሚ የማነቃቂያ እገዛ ለመስጠት የበለጠ እንዲነሳሱ ሊረዳ ይችላል፡፡

ሐ. በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር ማስተማር ሂደት በተነሳሽነትና በንባብ ትምህርት ውጤት መካከል ስለሚኖረው ተዛምዶ ለማወቅና ከዚህም ተጠቃሚ ለመሆን ለሚፈልጉ ተማሪዎች መምህራንና ተመራማሪዎች ጠቃሚ መረጃን ሊሰጥ ይችላል፡፡

መ. በንባብ ትምህርት እና በተነሳሽነት ዙሪያ የሚካሄደው ጥናት ቀጣይነት ያለው በመሆኑ ወደፊት ይህንን ርዕስ አስመልክቶ ለሚደረጉ ምርምሮች መነሻ ሊሆን ይችላል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከቦታ አንጻር በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት፣ በጅማ ዞን፣ በአጋሮ ወረዳ ፣ ከሚገኙ ሁለት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በጅዳ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ብቻ የተወሰ ነው።ይህ ትምህርት ቤት የተመረጠበት ምክንያት ካሉት ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በአብዛኛው የኦሮሚኛ አፍ ፈት ተማሪዎች መገኘታቸው እና የአማርኛ ቋንቋ ውጤታቸው ዝቅተኛ መሆኑ እንዲሁም ትምህርት ቤቱ በአጥኝዋ የመኖሪያ አካባቢ በመኖሩ ተገቢውን መረጃ በጊዜ እና በጥራት ለማግኘት አመቺ ስለሚሆን ነው። በተመረጠው ትምህርት ቤት ውስጥ በ2016ዓ.ም በ9ኛ ክፍል ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊዎች ናቸው። የ10ኛ ፣11ኛ፣ 12ኛ፣ ክፍል ተማሪዎችን አያካትትም ምክንያቱም ከተማሪዎች ብዛት ተገቢውን መረጃ በጊዜ እና በጥራት ከማግኘት አንፃር ችግር ሊያጋጥም ይችላል ከሚል ስጋት ነዉ።

ጥናቱ ከይዘት አንጻር የንባብ ትምህርት ተነሳሽነት ከአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት ጋር ያላቸውን ተዛምዶ በመፈተሽ ላይ የተወሰነ ነው። የንባብ ትምህርት ተነሳሽነት ነፃ ተለዋዋጭ ሲሆኑ የትምህርት ውጤት ተዛምዶ ጥገኛ ተለዋዋጭ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት የተማሪው ውጤት የንባብ ተነሳሽነት በመኖሩና ባለመኖሩ ላይ ጥገኛ በመሆኑ ነው።

ጥናቱ በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ላይ የሚያተኩር ሆኖ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የንባብ ክሂል ትምህርት ተነሳሽነት የውጤት ተዛምዶ ላይ ብቻ ተካሂዷል።

ጥናቱ የሚከተለው ተዛምዳዊ ስልት ነው። ምክንያም ያለው 1998 እንደገለጹት ተዛምዶዊ ጥናት በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ተለዋዋጮች መካከል ሊኖር የሚችልን የግኑኝነት አቅጣጫ እና መጠን ለመወሰን የሚያስችል ስለሆነ ነው። ጥናቱ በዋነነት ውስጣዊ፣ ውጫዊ፣ ውህዳዊ እና ጥቅማጥቅማዊ የተነሳሽነት አይነቶች ላይ ያተኩራል። ምክንያቱም እነዚህ ዋና ዋና የሚባሉት የተነሳሽነት አይነቶች በመሆናቸው ነው።

## 1.7. የቁልፍ ጽንሰ ሀሳቦች አጠቃቀም ብያኔ

1. ተዛምዶ (Correlation) ፡- የአፋን ኦሮሞ አፈ-ፈት ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ሲማሩ ቋንቋውን ለመማር ባላቸው ተነሳሽነትና በውጤታቸው መካከል የሚኖርን አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ግንኙነት ይመለከታል፡፡

1. ተነሳሽነት፡- የአፋን ኦሮሞ አፈ-ፈት ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት ሲማሩ ቋንቋውን ለመማር ያላቸው አመለካከት፣ ፍላጎት፣ ስሜት፣ ጉጉት፣ ምኞትና ጥረት ይመለከታል፡፡
2. የትምህርት ውጤት (Achievement):- አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ የአፋን ኦሮሞ አፈ-ፈት ተማሪዎች የሚኖራቸውን የተነሳሽነት መጠንና አይነት ተከትሎ በቋንቋው ፈተና ያስመዘገቡትን ውጤት ወይም ስኬት ይመለከታል፡፡
3. ውሳጣዊ ተነሳሽነት፡- የአማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ቋንቋውን
   እንዲያውቁ፣ እንዲረዱና በቋንቋው ለመግባባት እንዲችሉ የሚያደርግ ውስጣዊ ወይም ተፈጥሮአዊ የመገፋፋት ስሜት ሲታይባቸው ውስጣዊ ተነሳሽነት ይባላል፡፡
4. ውጫዊ ተነሳሽነት፡- አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ስለ ቋንቋው እንዲያውቁ፣ እንዲረዱና ለመግባባት እንዲችሉ በሚያደርጉ ውጫዊ ጥቅሞች አማካይነት ቋንቋውን ለመማር የሚያሳዩትን የመገፋፋት ስሜት ይመለከታል፡፡
5. ውህዳዊ ተነሳሽነት፡- በተነሳሽነት መለኪያ መሠረት አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ከአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ባህል ጋር ለመተሳሰር ያላቸውን ፍላጎትና ጥሩ አመለካከት ይገልጻል፡፡
6. ጥቅማጥቅማዊ ተነሳሽነት፡- በተነሳሽነት መለኪያ መሠረት አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ለተለያዩ ተግባራዊ ምክንያቶች ለምሳሌ፡- ስራ ለማግኘት፣ ፈተና ለማለፍ፣ እንዲሁም በቋንቋው ትምህርታዊና ኢኮኖሚያዊ አጋጣሚዎችን ለመጠቀም ቋንቋውን ለመማር የሚያሳዩትን ጥረት ይወክላል፡፡
7. የጽሁፍ መጠይቅ፡- በጽሑፍ ደረጃ ሊያዝ የሚችል አስተማማኝ የሆነ ጊዜን፣ ጉልበትንና ገንዘብን የሚቆጥብ የመላሾችን ማንነት የማይገልጽ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝት

### 2.1.1 የንባብ ምንነት

ማንበብ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ይበልጥ አስፈላጊ መሰረታዊ ከሆኑ ክህሎች ውስጥ አንዱ መሆኑን Lindesy and Niyet (2006) ያመለክታሉ፡፡በንባብ እውቀት ይዳብራል የተደበቀ ሀሳብን መርምሮ ለማግኘት አንድን ፅሁፍ መርምሮና አብራርቶ ለመረዳት ይረዳል፡
ንባብ በማንኛውም ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች እጅግ አስፈላጊና ወሳኝ የሆነ ክህል ነው፡፡ የተማሪዎች ስኬትም ሆነ ውድቅት የሚወሰነው በሚኖራቸው የግል የማንበብ ክሎት ወይም ችሎታ ነው፡፡በማለት Nilsun (1963 ) ያስረዳሉ፡፡

እንደJohan Atikens (1996) ንባብ ማለት መስተጋብራዊ ሂደት ነው፡፡ በማለት ይገልፃሉ ከዚህ የምንረዳው ንባብ ማለት በአንባቢያን እና በፀሀፊ መሀከል የሚደረግ የሀሳብ ግንኙነት ሂደት ነው፡፡Wiliyam (1984) ንባብ ማለት አንድ የተፃፈ ነገር አንብቦ የመገንዘብ ሂደት ነው፡ ፡በማለት ይገልፀዋል፡፡

እንደ Girlet (1981) ንባብ ማለት መገመት መተንብይ ማመሳከር እራስን ጥያቄ መጠየቅ እና ንቁ ተሳትፎ ማድረግ የሚፈልግ ሂደት ነው፡፡በሂደቱም አንባቢው ከምንባቡ አውድ በመነሳት የአዳዲስ ቃላት ፍቺዎችን የሚገመግምበት ገና ከመነሻው ባገኘው መረጃ ላይ በመመርኮዝ የምንባቡን ዋና ይዘትና ወደፊት ምን እንደሚገጥመው የሚተነብይበት ያነበበውን ፅሁፍ መረዳት አለመረዳቱን እራሱን የሚጠይቅበት በመጠየቅ የሚያመሳክርበት ሂደት መሆኑን እንረዳለን ፡፡

### 2.1.2.. የንባብ ትምህርት ዓላማ

Niwtel (1982) የንባብ ትምህርት ዓላማን ሲገልፁ ማንበብን በማስተማር ተማሪዎች የንባብ ልምድ እንዲኖራቸው ከማስቻል በላይ እንግዳ የሆኑ ፅሁፍ ቢያገጥማቸውም እንኳን ያለ አጋዥ በተገቢው ፍጥነት በጥሞናና በበቂ ግንዛቤ እንዲያነቡት ያስችሏቸዋል፡፡በማለት ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ የምንረዳው ተማሪዎች ከምንባብ በፊት ያላቸውን የንባብ ልምድ መሰረት አድርገው ወቅታዊና አዳዲስ ፅሁፎች ሲያጋጥማቸው ያላቸውን እውቀት ተጠቅመው ያለችግር ሀሳቡን ሊያብራሩና ሊጠቀሙበት መቻለቸው ነው፡፡

በተጨማሪም Giret (1990) የንባብ ትምህርት ዓላማን ሲያብራሩ ንባብን የምናስተምረው ተማሪዎች አጠቃላይ እውቀታቸውን ለማሳደግ እንዲችሉ መሰረታዊ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማሳደግ የአጠቃላይ እውቀት ይዘት ያላቸውን ፅሁፎች ማንበብና መረዳት እንዲችሉ ማስቻል ነው፡፡

## 2.1.3. አንብቦ የመረዳት ምንነት

አንብቦ መረዳት ማለት አንድን በፅሁፍ ፣በምልክት የቀረበን ጉዳይ ወይም ሁኔታ በዝርዝርና በጥልቀት ተመልክቶ ከራስ ጋር በማዋሀድ በማስተካከል አሊያም እንደየ ሁኔታው መልእክቱን የመቀበል ወይም ያለመቀበል ግንዛቤ መኖር መቻል ማለት ነው፡፡

አንብቦ መረዳትን አስመልክቶ Girlet (1981) አንብቦ መረዳት ማለት ከአንድ አሀድ ውስጥ የተፈለገውን መረጃ በብቃት ማሰባሰብ መቻል ማለት ነው፡፡በዚህ አይነት ሂደት ውስጥ አንባቢው የማይፈልገውን መረጃ እያንገዋለለ በመተው የሚፈልገውን አይነት ብቻ ሊመርጥ ይችላል፡፡ከዚህም በቀር የአንዳንድ አሀድ መሰረታዊ ሀሳብ ከመረዳትም ባሻገር ዝርዝሩን በብቃት የሚገነዘብበት ሁኔታ የሚጠቃለለው እዚህ ውስጥ ነው ይላሉ፡፡

ከዚህ ሀሳብ የምንገነዘበው በንባብ ወቅት ወይም ሂደት ከአንድ ከተሰጠ ወይም እንደተጠቀሰው ከአሀድ ውስጥ የሚፈለጉትን መረጃዎች በሙሉ ፈልፍሎ ማውጣት መቻል እንዳለብንና የሚፈለጉትን ከማይፈለጉት ለይትን በመተንተን በበቂ ሁኔታ መገንዘብ እንድሚገባ ያስረዳናል፡፡

የአንብቦ መረዳት መገለጫዎች ከሆኑት መካከል አንዱ ማስተዋል ነው ማስተዋል ብሎም መረዳት መቻል እንደየ ግለሰቡ የአእምሮ ብስለትና የአስተሳሰብ አድማስ ስፋት ደረጃው የተለያየ መሆኑን ከተጨባጭ ሁኔታ የሚንፀባረቅ እውነት ነው፡፡አንብቦ መረዳት ከሚገለፅባቸው መልክ ሌላው ደግሞ በፅሁፍ አጠቃላይ ገፅታ ወይም ስዕል ለማሳየትየመቻል ብቃቱ ነው፡፡ይህምአስቀድሞ አጠቃላይ የሆኑ ሀሳቦችን ወይም መገለጫዎችን በማቅረብ በመቀጠል ስለየአንዳንዱ ዝርዝር ሁኔታ በማስከተል ማንሳት የነገሩን ሁኔታ ወይም ምንነቱን ተፈጥሮውንም ሆነ መለያ ባህርያቱን ወዘተ በማቅረብ ስዕላዊ ገፅታውን ማቅረብ ይቻላል፡፡

እንደ Gernwood (1981) አገላለፅ አንብቦ መረዳት በአንድ ፅሁፍ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልክት መገንዘብ ነው፡፡በእያንዳንዱ ፅሁፍ ውስጥ ያለውን መልእክት ለመረዳት የእያንዳንዱን ቃል ፍቺ ማወቅ የግድ አይሆንም፡፡በፅሁፍ ውስጥ በግልፅ የተቀመጠውን መልክትና መልክቱን ለማጠናከር የገቡትን ዝርዝር ጉዳዮች መረዳት ግን ወሳኝ ነው፡፡

### 2.1.4.በአንብቦ መረዳት ተግባራት የክፍል ውስጥ ትግበራ ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎች

#### 2.1.4.1 የተማሪዎች ተነሳሽነት

እንደTirheri and Doctrew (2004) ገለፃ ተማሪዎች እራሳቸውን እንደ አንባቢ ካልቆጠሩ እና ምንባቡን ለምን እንደሚያነቡ አላማ ካላስቀመጡ የአንብቦ መረዳት ተግባር ላያ ተፅእኖ ያሳድራል፡፡Guthri (2006) ተማሪዎች ለአንብቦ መረዳት የሚያነሳሱ የተለያዩ ተግባራት እና ሁኔታዎች አለመኖር ወይም አነስተኛ መሆን መምህሩ የሚያነበውን ፅሁፍ አላማ ተማሪዎችን ለማነሳሰት የማይጠቀምበት ከሆነ የሚነበበው ፅሁፍ ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር ካልተመጣጠነ በአንብቦ መማር ትምህርቱ መምህሩ ጣልቃ እየገባ የተማሪዎችን አረዳድ ላይ ክትትል ካላደረገ ለተወሰነ ጊዜ የማንበብ ተነሳሽነትን የሚያመጡ እንደ ሽልማት ምስጋና እውቅና መስጠት እና የመሳሰሉት የማይደረጉ ከሆነ ወይም አነስተኛ ከሆነ ተፅኖ እንደሚያሳድር ገልፀዋል፡፡

#### 2.1.4.2 በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ብዛት

በአንድ የመማሪያ ክፍል ውስጥ ከሚፈለገው መጠን በላያ የተማሪዎች መኖር በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ችግር መፍጠሩ አይቀሬ ነው፡፡ Deighton (1971) እንደገለፁት ብዛት ያላቸው ተማሪዎች በሚማሩበት ክፍል ውስጥ ተማሪዎች የማዳመጥ ፣የመናገር ፣የማንብብ እና የመፃፍ ክህሎት የማጎልበት እድላቸው ዝቅተኛ ነው፡፡መምህሩም እያንዳንዱን ተማሪ የሚተገብረውን ለመከታተል ፣ድጋፍ ለማድረግ እና ተገቢ ግብረ መልስ ለመስጠት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

#### 2.1.4.3.የተማሪዎች ቅድመ እውቀት እና የቋንቋ ችሎታ መለየት

ስለሚነበበው ፅሁፍ በቂ ዳራዊ እውቀት የሌለው ተማሪ ፅሁፍን አንብበው የመረዳት ተነሳሽነታቸው አነስተኛ ነው፡፡ይህም ለመነበብ ከቀረበው ፅሁፍ ተጨማሪ እውቀት ለማግኘት የሚያደርጉትን ጥረት እና መከወን ያለባቸውን ተግባር ይገድባል፡፡እንደ Androwed 1987) አገላለፅ በአንድ የመማሪያ ክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች የተለያየ ዳራዊ እውቀት እና የቋንቋ ችሎታ እንደሚኖራቸው አያጠራጥርም በመማር ማስተማሩ ሂደት ይህን የመፈተሽ ተግባር ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

#### 2.1.4.4 አቀላጥፎ አለማንበብ

አቀላጥፎ ማንበብ አንባቢው ቃላትን ከፅሁፍ ጋር በማገናኘት በትክክል የማወቅ ፅሁፍን በተገቢው ሁኔታ እና ፍጥነት የማንበን እና የመረዳት ችሎታ ነው፡፡አቀላጥፎ የማንበብ

ደረጃ መድረስ አንባቢው መረዳት ላይ እንዲያተኩር የሚያስችል አላባ ነው፡፡በተቃራኒው አቀላጥፈው የማያነቡ ተማሪዎች ፅሁፉን በጥረጣሬ እና ያለ ስሜት ስለሚያነቡ በአንብቦ መረዳት ትምህርት አተገባበር ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ያሳድራል፡፡Onthario ( 2003)

### 2.1.5 የተነሳሽነት ምንነት

ተነሳሽነት የሚለዉን ስነ ልቦናዊ ጽንሰ ሃሳብ የተለያዩ ምሁራን በተለያየ መንገድ ብያኔዎችን ሲሰጡ ይስተዋላሉ፡፡ ከነዚህም ዉስጥ የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸዉ፡፡

Williams and burden (1997) እንደሚገልጹት ተነሳሽነት ንቁ በሆነ አእምሮ (በሙሉ ንቃተ ሂሊና) አንድን ድርጊት ለመፈጸም የሚካሄድ ጥረትን የሚያበረታታ አእምሮታዊ እና ስሜታዊ ቅስቀሳ ነዉ፡፡

Brown (2000) የተነሳሽነት ምንነትን ከሚከተሉት እይታዎች አንጻር ብያኔአቸዉን ያስቀምጣል

ተነሳሽነት ከባህሪያዉያን እይታ አንጻር አንድን ተግባር ለማከናወን ማጠናከሪያ ሰጥቶ ምላሽ እንዲሰጥ ከማድረግ ጋር የተያያዘ ነዉ ፡፡ ከአእምሮታዉያን አኳያ በዚህ እይታ መሰረት ተነሳሽነት የሚመነጨዉ ከራሱ ከግለሰቡ ነዉ፡፡
ይህ እይታ ከግንባታዉያን አንጻር በማህበራዊ አዉድ እንዲሁም በግለሰቦች ምርጫ ላይ የተመሰረተ ነዉ፡፡ ባጠቃላይ በሶስቱ መካከል ያለዉን የተነሳሽነት እይታዎችን Brown (2000) በሚከተለዉ መልኩ ያስቀምጡታል፡፡

ሰንጠረዠ ሀ ከተነሳሽነት አንጻር ባህሪያዉያን፤ አእምሮታዊያን እና ግንባታዉያን ያላቸዉ እይታ፡፡

| ባህሪያዉያን | አእምሮታዉያን | ግንባታዉያን |
|---|---|---|
| ማጠናከሪያ(ሽልማት) በመስጠት ላይ የተኩራል | በግለሰቡ ፍላጎት ላይ ይመሰረታል | ማህበራዊ አዉድ ላይ ይመሰረታል |
| በዉጫዊ ሁኔታዎች ወይም ግለሰቦች ቁጥጥር ስር ነዉ | ዉስጣዊ በመሆኑ በግለሰቡ ይመራል | ዉስጣዊ ሆኖ በተራክቧዊ ሁነቶች ላይ ይመሰረታል |

ከላይ የቀረበዉ ሰንጠረዥ ተነሳሽነት የሚፈጠርበትን መንገድ በተመለከተ በሶስቱ እይታ ምን እንደሚመስል ያሳያል፡፡ ይህም በቋንቋ ትምህርት ሂደት ዉስጥ ስታይ ለተማሪዉ

ማበረታቻ ወይም ማጠናከሪያ እየተሰጠዉ የሚማር ከሆነ በባህሪያዉያን እይታ ተነሳሽነቱ ከፍተኛ እየሆነ እንደሚሄድ የሚያመለክት ነዉ፡፡

በሌላ መልኩ በቋንቋ ትምህርት ሂደት ያለምንም ዉጫዊ ተጽዕኖ በግለሰቡ ዉስጣዊ ፍላጎት ከፍ ወይም ዝቅ ሊል ይችላል የሚሉት ደግሞ አእምሮያታዉያን ናቸዉ፡፡ በተጨማሪም በግምባታዉያን አተያይ ተማሪዉ በቋንቋ ትምህርት ሂደት ባለዉ ዉስጣዊ ተፅዕኖ እና በሚያከናዉነዉ ማህበራዊ ተራክቦ በተነሳሽነቱ ላይ በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ መንገድ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

### 2.1.6 የተነሳሽነት ዓይነቶች

የተለያዩ ምሁራን የተነሳሽነት ዓይነቶችን በተለያየ መንገድ ሲከፋፍሏቸዉ ይታያል፡፡ Brown (2000) Deci (1975)ን በመጥቀስ የተነሳሽነት ዓይነቶችን በሁለት ከፍለዉ ያስቀምጧቸዋል፡ ፡ እነሱም ዉስጣዊና ዉጫዊ ተነሳሽነት ናቸዉ፡፡

ዉስጣዊ ተነሳሽነት፡- ዉስጣዊ ተነሳሽነት ያለዉ የቋንቋ ተማሪ ታላሚዉን ቋንቋ የሚማረዉ በተማረዉ ቋንቋ አንዳች ጥቅምን ለማግኘት ፈልጎ ወይም ሌላ ከበስተጀርባዉ የሚገፋፋዉ ኃይል ኖሮ ሳይሆን ቋንቋዉን በመማሩ ከሚሰማዉ እርካታ በመነሳት በግሉ ልዩ ልዩ ትምህርታዊ ተግባራትን ለማከናወን ጥረት የሚያደርግበት ነዉ፡፡ በመሆኑም ይህ የተነሳሽነት ዓይነት ተማሪዉ ከዉስጡ ከሚመነጭ ፍላጎት በመነሳት በታላሚዉ ቋንቋ የተምህርት ሂደት ላይ ተሳታፊ የሚሆንበት ነዉ፡፡

**ዉጫዊ ተነሳሽነት**፡-በዉጫዊ ተነሳሽነት ተማሪዉ ቋንቋዉን የሚማረዉ ከዉስጡ በመነጨ ስሜት ሳይሆን የሌሎችን ድጋፍ ወይም ማበረታቻ በመፈለግ ነዉ፡፡ ይህ የተነሳሽነት ዓይነት በዋነኝነት የሚመሰረተዉ በዉጫዊ ድጋፍ በመሆኑ የተነሳ ማበረታቻ እና እገዛ ለተማሪዉ የማይደረግለት ከሆነ በትምህርቱ ሂደት የመዳከም ሁኔታን ያሳያል፡፡

በሌላ መልኩ krashen (1988) ተነሳሽነትን ጥምረታዊ እና ቁሳካላዊ በማለት ከፍለዉ ያስቀምጡታል፡፡

**ጥምረታዊ ተነሳሽነት**፡-ከቋንቋ መማር አንጻር ያለዉን ሚና ሲታይ በጣም ጠንካራ የሆነ የተነሳሽነት ዓይነት ነዉ፡፡ ይህ ተነሳሽነት ያላቸዉ ተማሪዎች ቋንቋዉን የሚማሩት ፈልገዉትና ይሁነኝ ብለዉ ስለሆነ የታላሚዉን ቋንቋ ታናጋሪዎች ባህል ወግና ልማድ በፍጥነት ለማወቅና ለመረዳት ብዙ አይቸገሩም፡፡ ዓላማቸዉም ከታላሚዉ የቋንቋ ማህበረሰብ

ጋር ስኬታማ ተግባቦትን መፍጠር በመሆኑ ከትምህርቱ ባሻገር የማህበረሰቡን የስነ ጽሑፍ ዉጤቶች ያነባሉ፤ እንዲሁም በተለያዩ ማህበራዊ ሕይወቶች ላይ ይሳተፋሉ፡፡

ሁለተኛዉ የተነሳሽነት ዓይነት ቁሳካላዊ አካላዊ መሳሪያዊ ተነሳሽነት ነዉ፡፡ ከሚያመጣዉ ዉጤት አንጻር ሲታይ ደካማ የተነሳሽነት ዓይነት ነዉ፡፡ እንደ ጥምረታዊ ተነሳሽነት ከራስ በሚመነጭ ፍላጎት ሳይሆን ቋንቋዉን የሚማረዉ በኣስገዳጅ ሁኔታዎች ወይም በመማሩ የሚያገኘዉን ጥቅም በማሰብ ነዉ፡፡ ከእነዚህም ምክንያቶች መካከልም ቋንቋዉን ተምሮ ሥራ ለመያዝ ፣ፈተና ለማለፍ፣ ጉብኝቶችን ለማድረግ ወዘተ--- የሚጠቀሱ ናቸዉ፡፡
እላይ ከተገለጹት የተለያዩ ምሁራን አስያየት መረዳት እንደሚቻለዉ ተነሳሽነት የተለያዩ አላማዎችን መሰረት በማድረግ አንድ ነገር ለምን እና እንዴት እደሚተገበር የሚያሳይ የባህሪይ ተፅዕኖ ሊያመጣ የሚችል ዉስጣዊ ግፊት ነዉ፡፡

### 2.1.7 ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት አይነቶች

ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ታላሚዉን ቋንቋ የሚማሩበት የራሳቸዉ የሆነ አላማ አላቸዉ፤ ይህን አስመልክቶ በሁለተኛ ቋንቋ መማር ተነሳሽነት ላይ ምርምር ካካሄዱት ተመራማሪዎች ቀዳሚ የሆኑት Gardner and Lambert (1972) የሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነትን ዉህዳዊና ጥቅማጥቅማዊ በማለት በሁለት ይከፍሉታል፡፡

ዉህዳዊ ተነሳሽነት የታለሚዉ ቋንቋ ተማሪዎች ከቋንቋዉ ተናጋሪ ማህበረሰብ አባላትጋር ዉህደት ወይም ቅርርብ ለመፍጠር በማሰብ ቋንቋዉን ለመማር ወይም ለማጥናት የሚነሱበት የተነሳሽነት አይነት ነዉ፡፡Gardenr (1972) ተማሪዎቹ ቋንቋዉን የሚማሩት ከቋንቋዉ ተናጋሪዎች ጋር ዉህደት ለመፍጠር በመሆኑ ቋንቋዉን የመማር ተሳትፏቸዉ የተወሰነ ስርአተ ትምህርት ሲጠናቀቅ የሚቋረጥ እንደማይሆን Gardener (1972) ያብራራሉ፡፡

ሁለተኛዉ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የተነሳሽነት አይነት ደግሞ ጥቅማጥቅማዊ ተነሳሽነት ነዉ፡፡ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በታላሚዉ ቋንቋ ተግባራዊ ወይም ተጨባጭ ጥቅማ ጥቅም ለማግኘት ቋንቋዉን የሚማሩበት የተነሳሽነት አይነት ነዉ Ellis.(1997) Gardener(1985)፡፡ ተማሪዎች ታላሚዉን ቋንቋ የሚማሩበት አላማ የተለያዬ ቢሆንም በአብዛኛዉ ግን የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም የዩኒቨርሲቲ መግቢያ መስፈርት ማሟላት የተሻለ ክፍያ ወይም ደሞዝ ማግኘት፤አለማቀፋዊ መረጃና እዉቀት ማግኘት የሚሉት ዋና ዋና የጥቅማጥቅማዊ ተነሳሽነት አላማዎች መሆናቸዉን Noris (2001) ያስረዳሉ፡፡

ሶስተኛዉ ዉስጣዊ የተነሳሽነት አይነት ነዉ። ዉስጣዊ ተነሳሽነት የሚባለዉ የተነሳሽነት አይነት በስነ ልቦና ትምህርት ዉሰጥ ከብዙጊዜ ጀምሮ የታወቀ እንደሆነ Ellis (1994) ይገልፃሉ።ዉስጣዊ ተነሳሽነት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ታላሚዉን ቋንቋ ከዉስጥ በሚመነጭ ግፊት የመማር ተግባራትን በማከናወን የሚገኝ የተነሳሽነት አይነት ነዉ፤

ተማሪዎች የመምህሩ የማስተማር ዘዴ ቢመቻቸዉም ባይመቻቸዉም ትምህርቱ ፈተና ቢኖረዉም ባይኖረዉም ቋንቋዉን ከመማር ወደኂላ አይሉም። ቋንቋዉን በመማር ሆነ ተግባራቱን በማከናወን ይረካሉ። ዉስጣዊ ተነሳሽነት ያላቸዉ ተማሪዎች የሚቀርቡላቸዉ የመማር ተግባራት አሰቸጋሪ ቢሆኑም እንኳን ተግባራቱን በማከናወን ይደሰታሉ።ዉጫዊ ማነሳሻ ወይም የመምህሩ ግፊትና ጉትጎታ ሳያስፈልጋቸዉ ከራሳቸዉ የሚመነጭ የመስራት ፍላጎት ይኖራቸዋል Noels ,(2003). Ur, (1996).

አራተኛዉ የተነሳሽነት አይነት ዉጫዊ ተነሳሽነት ነዉ፡ይህ በመምህራን ፤በወላጆች ፤ በጓደኞች ወይም በሌላ አካል ለመወደስ ፤ሽልማት ለማግኘት ፤ለመመስገን ፤በፈተና ጥሩ ዉጤት ለማስመዝገብ ፤ጥፋት በመቀነስ ቅጣት ለማስቀረት ያሉ የአጭር ጊዜ ግቦችን የሚያስገኝ የተነሳሽነት አይነት ነዉ።Elliot ,and others ,(2005).Brawon,(1994).

በአጠቃላይ በዘሪቱ(2003)። የተጠቀሱት Gardenere-(1985)እንደሚያስረዱት በሁሉም የተነሳሽነት አይነቶች አንድን ግለሰብ ተነሳስቷል ለማለት ሁለት ነገሮችን መሰረት ማድረግ ያስፈልጋል።የመጀመሪያዉ ግለሰቡ አላማ ተኮር የሆነ እንቅስቃሴ ሲያሳይ ሲሆን ሁለተኛዉ ደግሞ ግለሰቡ ጥረት የሚታይበት ከሆነ ነዉ፤በዚህ ሁኔታ ዉስጥ ያለ ግለሰብ ስለሚያከናዉኗቸዉ ተግባራት ቢጠየቅ ለዚሁ አላማ ያለዉን ምኞት ወይም ፍላጎትና ቋንቋዉን መማር ለሚያስችሉ ተግባራቱ ያሉትን ጥሩ አመለካከቶች ያንጸባርቃል፡ ከዚህም በመነሳት ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት አራት ሁኔታዎችን ያካተተ ነዉ ለማለት ይቻላል እነዚህም ሁለተኛ ቋንቋን የመማር ግብ ፤ጥረት የተሞላበት ባህሪ፤አላማን የማሳካት ምኞትና ለሚከናወነዉ ተግባር የሚኖሩ ጥሩ አመለካከቶች ናቸዉ Gardener(1985) አክለዉ እንደሚያብራሩት ከላይ የሰፈሩት ሁለተኛ ቋንቋን የመማር ተነሳሽነት ሁኔታዎች ከፅንሰ ሀሳብ አኳያ በሁለት ምድቦች ይከፈላሉ። በክፍፍሉ የመጀመሪያው ምድብ ግብ ነው። ለተነሳሽነት ግብ ምክንያት ወይም የሚገፋፉ ነገር ቢሆንም በግለሰቦች መካከል ያለን መለያየት አያንፀባርቅም፤ከተነሳሽነት፡ አንፃርም ሊለካ፡ አይችልም ፤ ግብ የሚንፀባረቀው ፡ ግለሰቡ ሁለተኛ ቋንቋውን ለማጥናት በሚኖረው ዝንባቤ ነው። በሁለተኛው ምድብ የተቀመጡት ጥረት የተሞላበት ፡ ባህሪይ ’ ዓላማን የማሳካት ምኞትና ለሚከናወነው ተግባር የሚኖሩትን ጥሩ አመለካከቶቶችን የሚመለከት ነው። በእነዚህ ሶስት

ሁኔታዎች በግለሰቦች መካከል ልዩነት ይንፀባረቃል። ሁኔታዎቹም በቀጥታ ሊለኩ ይችላሉ። ስለሆነም ሁለተኛ ቋንቋ ፡ የመማር ተነሳሽነትን፡ መመርመር ከውህዳዊም፡ ሆነ፡ ከጥቅማጥቅማዊ የዝንባሌ ዓይነቶች ጋር ግንኙነት ሊኖራቸውም ላይኖራቸውም የሚችሉ ሶስት ውስብስብ ባህርያትን መመልከት ያስችላል። እነዚህ ውስብስብ፡ ባህሪያት ወይም ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት አላባዉያን የሚባሉት ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋውን ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት የሚባሉት መጠን ወይም ጥረት ፤ ሁለተኛ ቋንቋውን የመማር ዓላማን የማሳካት ምኞትና ሁለተኛ ቋንቋውን፡ ለመማር የሚኖር ጥሩ አመለካከት ናቸው።

### 2.1.8. ተነሳሽነት ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ጋር ያለው ተዛምዶ

ታላሚውን ቋንቋ የመማር ፍላጎትና ምኞት ያደረበት ተማሪ ጥረት ካሳየ በቋንቋ ፈተናው ፡ ጥሩ ውጤት እንደሚያስመዘግብ፡ ይታመናል ፤በቋንቋው የመጠቀም ጥሩ ችሎታም ሊኖረው ይችላል። በተነሳሽነት ዙሪያ ከተከናወኑት የምርምር ስራዎች መካከል እያንዳንዱ የተነሳሽነት ዓይነት ከትምህርት ውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ በሚመለከት ረገድ የመጀመሪያው ምርምር Gardner and Lambert (1972) በፊሊፒንስ የተካሄደ ጥናት ነው Brown, (2000). Ellis (1994). ተነሳሽነት ከውጤት ጋር ያለው ተዛምዶም በአራት ምድብ ይታያል።

#### 2.1.8.1. ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት

ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ላይ በተካሄደው ምርምር ጋርድነርና ፡ ላምበርት የፊሊፒንስ ተማሪዎች የእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቃታቸውን ለማሳደግ ሲያሳዩ የነበረው ጥረት ከእንግሊአኛ ተናጋሪ ሕዝቦች ጋር ውህደት ወይም ትስስር ለመፍጠር ሳይሆን በቋንቋው ጥቅማ ጥቅም ለማግኘት እንደነበር Brown ፣(2000)። ያስረዳሉ። በመሆኑም Gardner and Lambert ከፊሊፒንሱ፡ የጥናት ግኝታቸው በመነሳት በጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ሁለተኛ ቋንቋን ውጤታማ በሆነ መልኩ መማር እንደሚቻል አረጋግጠዋል። Brown (2000) Ellis (1994)፡ ፡ በተመሳሳይም በክሌ ፣(1994) ዋቢ የተደረጉ Fishman(1977)። ዕብራይስጥኛ ቋንቋ በሚናገሩ በእስራኤል ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ላይ ያካሄዳቸው ምርምሮች ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተሻለ ብቃት ማሳየታቸውን አረጋግጠዋል። ከዚህም በመነሳት ታላሚው ቋንቋ አለም አቀፋዊ የመግባቢያ ይዘትነት ካለው ጥቅማጥቅማዊ ዓላማን መሰረት ያደረገ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤታማ ሊያደርግ ይችላል በሚል ደምድመዋል።

#### 2.1.8.2. ውህዳዊ ና ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት

በEllis፣ (1994)። የተጠቀሱት walf ፣(1982)። በአሜሪካ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ የስፔይን ተወላጅ ተማሪዎች በውህዳዊና ጥቅማ ጥቅማዊ መለኪያ

ጥያቄዎች ተጠይቀው ለሁለቱም የተነሳሽነት ዓይነቶች ጥሩ አመለካከት  አሳይተዋል፡፡ የውጭ  ቋንቋ የሚያጠኑ ተማሪዎች በአብዛኛው ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ወይም ዓላማን ታሳቢ በማድረግ  ቋንቋውን ይማራሉ፡፡

Noels ፣(2001)፡፡ እንደሚገልፁት ውህዳዊና ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነቶች ሁለቱም ውጫዊ ዓላማዎችን ለማሳካት ማለትም ውህዳዊ ተነሳሽነት ከቡድኖች ጋር ማህበራዊ ውህደት ለመፍጠር ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ደግሞ ተጨባጭ ሽልማትን ተስፋ ስለሚያደርግ ተመሳሳይ ባህሪይ እንዳላቸው ያስረዳሉ፡፡

### 2.1.8.3. ውስጣዊና ውጫዊ ተነሳሽነት

Brown (2000) እንደሚገልጹት ውስጣዊና ውጫዊ የተነሳሽነት አቅጣጫዎች በአብዛኛው በዉጪ ቋንቋ መማሪያ ክፍሎች ውስጥ ተግባራዊ የሚሆኑ ናቸው፡፡ ከሁለቱ የተነሳሽነት ዓይነቶች ውስጣዊ ተነሳሽነት በቋንቋ ትምህርት ውጤታማ እንደሚያደርግና በተለይም ለረዥም ጊዜ ትውስታ አስፈላጊ መሆኑን ያብራራሉ፡፡

Noels፣ (2001)፡፡ ውስጣዊ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች የጭንቀት መጠናቸው ዝቅተኛ ይሆናል፡፡ ስለሚማሩት ቋንቋ አዎንታዊ አመለካከት ይኖራቸዋል፡፡ እንዲሁም ቋንቋ የመማር ብቃታቸውም ይጨምራል በማለት ያብራራሉ፡፡ የአማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ ተማሪዎች ላይ በክፍሌ (2002) በተከናወኑት ጥናቶችም በውስጣዊ ተነሳሽነትና በትምህርት ውጤት መካከል ጉልህ ተዛምዶ መኖሩ ተመልክቷል፡፡ በሌላ በኩል Noels (2001) ውስጣዊም ሆነ ውህዳዊ የመማር ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች ለሚማሯቸው የትምህርት ተግባራት እና ለመማር ሂደቱ አውንታዊ አመለካከቱ ስለሚኖራቸው ሁለቱ የተነሳሽነት ዓይነቶች ተመሳሳይነት እንዳላቸው ይስማማሉ፡፡

ሰንጠረዥ  ለ የውስጣዊና የውጫዊ ተነሳሽነት ንጽጽር

| ተ.ቁ | ውስጣዊ ተነሳሽነት | ውጫዊ ተነሳሽነት |
|---|---|---|
| 1 | ስኬት በውስጣዊ መስፈርት ይወሰናል፡፡ | ስኬት በውጫዊ ተነሳሽነት ይወሰናል፡፡ |
| 2 | ከውስጥ ፍላጎትና ጉጉት ይመነጫል፡፡ | በሌላ አካል ከሚቀርብ ምስጋና ሽልማት ወዘተ ይመነጫል፡፡ |
| 3 | አድካሚ ተግባር ለማከናወን መፈለግን ይመለከታል፡፡ | ቀላል ተግባር ለማከናወን መፈለግን ይመለከታል፡፡ |
| 4 | ችግሮችን በግል መፍታት ያስችላል፡፡ | ችግሮችን ለመለየትና በችግሮች ላይ ለመወሰን በመምህር ላይ ጥገኛ ያደርጋል፡፡ |
| 5 | የረዢም ጊዜ ግብን ወይም አላማን መሰረት ያደርጋል፡፡ | ያጭር ጊዜ ግብ ወይም አላማ አለው፡፡ |

## 2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአጋሮ ከተማ ፣በጅዳ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2016 ዓ.ም 9ኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች ለንባብ ትምህርት ያላቸው ተነሳሽነት ከውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ መርምሮ የመፍትሔ ሀሳብ ለመስጠት ነው፤ በመሆኑም ከጥናቱ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተዛማጅነት ያላቸው ቀደምት ጥናቶችን በሚከተለው መልኩ ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

እንዳሀገራችንም ርእሰ ጉዳዩን በሚመለከት ተዛማጅነት ያላቸው ቀደምት ጥናቶች እንደሚከተለው ታይተዋል፡፡

የመጀመሪያው ተዛማጅ ጹሑፍ የስመኝ (2002) ‹‹በሁሩሙ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው ተነሳሽነት›› በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የቀረበ ጥናት ውጤት ነው፡፡ ስመኝ ለጥናቱ ማከናወኛ የመረጣቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳርያዎች የጹሑፍ መጠይቅ’ የቃል መጠይቅና ምልከታ ናቸው፡፡ የተሰበሰቡትም መረጃዎች ዓይነታዊ የመተንተኛ ዘዴን ተጠቅሞ ሲሆን በጥናቱ ውጤት የተማሪዎች ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆኑንና ዝቅተኛ ለመሆኑ ምክንያቱ የመማሪያ መጻሕፍትን በሚመለከት የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት ያላገናዘበ እንደሆነ በተጨማሪም በተማሪዎች ተነሳሽነት ዙሪያ የመምህራን ተሳትፎ የቀዘቀዘ መሆኑን በመግለጽና ለወደፊት በትምህርቱ ሂደት በተማሪዎች ተሳትፎ ላይ ትኩረት ሊደረግበት እንደሚገባ በማሳሰብ ጥናቱን አጠናቋል፡፡

የስመኝ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነትም ልዩነትም አለው፡፡ ልዩነቱ የእርሱ ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀማቸው መሳሪያዎች ምልከታ ፣ የጹሐፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ ሲሆን ይኸኛው ጥናት የጹሑፍ መጠይቅ ምልከታና ፈተናን በመረጃ መሰብሰቢያነት ተጠቅሟል፡፡ ሌላው ልዩነት የዓላማ ልዩነት ነው፤ የእርሱ ጥናት ዓላማ በተማሪዎች ተነሳሽነት ላይ ትንተና ማቅረብ ሲሆን የዚህኛው ጥናት ዓላማ ግን የንበብ ክህል ተነሳሽነት ከውጤት ጋር ያለውን ዝምድና መፈተሽ ነው፡፡ጥናቶቹ በዘመንም ይለያያሉ፡፡በሌላ መልኩ የስመኝና ይኸኛው ጥናት ሁለቱም ስለተነሳሽነት ይዘዉ ቢነሱም ይሄኛዉ ጥናት የንባብ ተነሳሽነት ከዉጤት ጋር ያለዉን ዝምድና መፈተሽ ስለሆነ ልዩተት ያሳያል፡፡
ሁለተኛው ተዛማጅ ጽሑፍ ዘሪቱ (2003) በአርባ ምንጭ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በጋሞኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት የውጤት ተዛምዶ በሚል ርዕስ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ

ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናትና ምርምር ውጤት ነው፡፡ ጥናቱን ከግብ ለማድረስ የጽሑፍ መጠይቅና ፈተናን በመጠቀም መረጃዎችን ሰብስባለች፤ የተሰበሰቡትንም መረጃዎች ገላጭ መጠናዊ የምርምር ስልትን በመጠቀም ተንትና በተደረገው ጥናት አማካኝነት የተማሪዎቹን የመማር ተነሳሽነት ከውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ ዝቅተኛ መሆኑን ገልጻለች፡፡ ይህም ማለት ተማሪዎቹ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከፍተኛ የሆነ መነሳሳት ቢኖራቸውም የፈተና ውጤታቸው ግን ከተነሳሽነታቸው ጋር መመጣጠን አለመቻሉ ነው፡፡

ለተማሪዎች የተነሳሽነትና ውጤት ተዛምዶ ልዩነት መፈጠር እንደ ምክንያት ያስቀመጠችው ለተማሪዎቹ የሚቀርብላቸው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጾታን' የክፍል ደረጃንና ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነትን መሰረት ያለማድረጉ መሆኑን ገልጻ በተጨማሪም ትምህርቱ ጥቅማ ጥቅማዊ የመማር ተነሳሽነትን በሚያበረታታ መልኩ የሚቀርብ ቢሆን ተማሪዎቹ የበለጠ ውጤታማ እንደሚሆኑ በመጠቆም አስተያየትዋን ሰጥታ ጥናትዋን አጠናቃለች፡፡

የዘሪቱ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር በሚከተሉት ጉዳዮች ይለያያል፡፡ በእርስዋ ጥናት ላይ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተነሳሽነት ከውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ ለመፈተሽ በጾታና በክፍል ደረጃ ልዩነት ስታጠና ይኸኛው ጥናት ግን የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ክሂል ትምህርት ከውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ በአንድ ክፍል ደረጃ ብቻ (በ9ኛ ክፍል) መሆኑ በተጨማሪም ጥናቱ የተካሄደበት ቦታና ጊዜ የተለያየ መሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር እንዲለያይ ያደርገዋል፡፡ እንዲሁም ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ለመረጃ መሰብሰቢያነት የጽሑፍ መጠይቅና ፈተና መጠቀሟ ነው፡፡

ሶስተኛው ተዛማጅ ጽሑፍ ጀማል (2001)፡፡ "በሴሩ አባስ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት ትንተና››በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የቀረበ ጥናትና ምርምር ውጤት ነው፤ በጥናቱ ክንዋኔ የተጠቀመባቸው መረጃ መሰብሰቢያ መሳርያዎች የጹሑፍ መጠይቅና ምልከታ ናቸው፡፡ የሰበሰባቸውን መረጃዎች አይነታዊ የመተንተኛ ዘዴ ተጠቅሞ የተነተነ ሲሆን በጥናቱ ሂደት የተማሪዎች ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆኑና ለዝቅተኛነቱ ምክንያት ናቸው ያላቸውን የመማሪያ መጻሕፍት በተመለከተ የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት አለማገናዘቡን፤ በተጨማሪም መምህራን ተማሪዎችን ለማሳተፍ የሚያደርጉት ጥረት ውስን እንደሆነ ገልፆ በትምህርቱ ሂደት ለተማሪዎች መነሳሳት ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ በማሳሰብ ጥናቱን ደምድሟል፡፡

የጀማል ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚለያይበት ነገር አለው፡፡ ይኸውም እርሱ ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀመባቸው መሳርያዎች የጹሑፍ መጠይቅና ምልከታ ብቻ መሆናቸውይህኛው ጥናት የችሎታ መለኪያ ፈተና መጠቀሙ አንደኛው ልዩነት ሲሆን ሁለተኛው ልዩነት ደግሞ የዓላማ ልዩነት ነው፡፡ የእርሱ ጥናት ዓላማ በተማሪዎቹ ተነሳሽነት ላይ ትንተና ማድረግ መሆኑና ጥናቱ የተካሄደበት ቦታና ዘመን በሴሩ አባስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 2001 ዓ.ም መሆኑ ሌላው ልዩነት ነው፡፡ ጥናቱ ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰልበት ይህኛው ጥናት ከተጠቀመበት የመረጃ መሰብሰቢያ ውስጥ የጽሑፍ መጠይቅ ምልከታ መጠቀሙ እንዲሁም በክፍል ደረጃው ይመሳሰላል፡፡

ተስፋዬ ኦላና (2014) በኢሊባቦር ዞን በሁሩሙና በሶንጦ 2ኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው ተነሳሽነትና የውጤት ተዛምዶ በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ምርምር ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀማቸው ዘዴዎች የጽሑፍ መጠይቅና ፈተና መጠቀሙ ያመሳስለዋል ልዩነቱ የተስፋዬ ጥናት አጠቃላይ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተነሳሽነት ከውጤት ጋር ያለው ተዛምዶ ሲሆን ይህኛው ጥናት ግን በአማርኛ ቋንቋ የንባብ ክሂል ያላቸው ተነሳሽነትና ከውጤት ጋር ያለው ተዛምዶ መፈተሽ መሆኑ ልዩ ያደርገዋል፡፡

ዮሀንስ ሰለሞን (2013) በአማርኛ ቋንቋ ኢ-አፍ ፈት የሆኑ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ ትንተና በጉጂ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት በሚል ርእስ በጅማ ዩኒቨርስቲ ለሁለተኛ ድግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ምርምር ሲሆን አላማው የተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነተ ተዛምዶ መፈተሽ ነው፡፡መረጃውን የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና እና የመምህራን ቃለ-መጠይቅ በመጠቀም ሰብስቧል የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ እንደሆነና የንባብ ፍጥነታቸውም ዝቅተኛ በሚባል ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አሳውቋል፡፡ በዚህም መሰረት አንብቦ መረዳት እና የንባብ ፍጥነት መካከለል ተዛምዶ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡

ይህን ጥናት ከዚህኛው ጥናት ጋር የሚያመሳስለው የንባብ ትምህርት ላይ ማተኮሩ ለመረጃ መሰብሰቢያነት የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና መጠቀሙ ያመሳስለዋል፡፡ ልዩነቱ ደግ የክፍል ደረጃ ይህኛው ጥናት በዘጠነኛ ክፍል ላይ ሲያተኩር የዮሀንስ በአስረኛ ክፍል ላይ ያተኩራል፡፡እንዲሁም ይህኛው ጥናት የንባብ ተነሳሽነት ከውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ ላይ ሲያተኩር የዮሀንስ ጥናት አንብቦ መረዳት እና የንባብ ፍጥነት መካከል ያለውን ተዛምዶ ይመለከታል፡፡

በአጠቃላይ ስመኝና ጀማል ጥናታቸውን ያካሄዱት በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሲሆን የዘሪቱ ጥናት ግን በዘጠነኛና በአሰረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው፡፡

ስለዚህ አጥኚዋ በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በንባብ ክህል ትምህርት ላይ የተማሪዎች ተነሳሽነትን ከዉጤታቸወ ጋር ያለዉን ተዛምዶ አስመልክቶ ማጥናት በተለያዩ ተመራማሪዎች የተጠቀሰውንና ለኢ-ስኬታማነት መንስኤ የሚሆነውን ችግር በማቃለል ተማሪዎችን ለስኬታማነት ያመቻቸል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የጥናቱ ዘዴና አካሄድ

## 3.1. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት ተዛምዶአዊ የምርምር ዘዴን ተከትሎ ተካሂዷል፡፡ ተዛምዶአዊ የምርምር ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት ተማሪዎቹ ለንባብ ትምህርት ያለቸዉ የመነሳሳት ሁኔታና ተነሳሽነታቸዉ ደግሞ ከትምህርት ዉጤታቸዉ ጋር የሚኖረዉን ዝምድና ለመለየት ተስማሚ በመሆኑ ነዉ፡፡

### 3.1.1.የጥናቱ አካላይ

ይህ ጥናት በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በጅማ ዞን በአጋሮ ወረዳ ከሚገኙ ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በጅዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተካሄደ ሲሆን ጥናቱ የሚያካልለው በ2016 ዓ.ም በዘጠነኛ ክፍል ተሚማሩ ተማሪዎች ለንባብ ክሂል ትምህርት ያላቸውን ተነሳሽነት ከውጤትታቸው ጋር ያለውን ተዛውዶ መፈተሽ ላይ ያካለለ ነው፡፡

### 3.1.2. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን አማርኛ የማንበብ ተነሳሽነትና የውጤት ተዛምዶን መመርመር የጥናቱ ዋና ዓለማ ነው፡፡ ለዚህም በጅማ ዞን በአጋሮ ወረዳ ውስጥ ከሚገኙት ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የጅዳ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአመቺ ናሙና ዘዴ ተመርጧል፡፡በአመቺ ናሙና ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት ትምህርት ቤቱ በአጥኝዋ የመኖሪያ አካባቢ በመገኘቱ ተገቢዉን መረጃ በጊዜ እና በጥራት ለማግኘት አመቺ ስለሆነ ነው፡፡

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለጥናቱ የተመረጡበት ምክንያት ከ1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ይልቅ መረጃዎችን በተሻለ ሁኔታ ሊሰጡ ይችላሉ የሚለውን ግምት ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ ይህም Brown (1994) ከህፃናት በተሻለ ስለ አፍ መፍቻና ሁለተኛ ቋንቋ ያላቸውን አመለካከትና ተነሳሽነት ሊያንፀባርቁ የሚችሉት በዕድሜ ከፍ ያሉ ተማሪዎች ናቸው ካሉት ጋር ተደጋጋፊ ነው፡፡ አብዛኛዎቹ ቀደምት ጥናቶች የተከናወኑትም ሁለተኛ ደረጃ በሚማሩ ተማሪዎች ላይ መሆኑ ደግሞ ተጨማሪ ምክንያት ነው፡፡ በጥናቱ ተሳታፊ የሆኑ ተማሪዎች በ2016 ዓ.ም 9ኛ ክፍል የሚማሩ የአፋን ኦሮሞ አፍ- ፈት ተማሪዎች ናቸው፡፡ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የተመረጡበት ምክንያት በዚህ ደረጃ ላይ ያሉ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ስለሆነ በሚቀጥለው ደረጃ በንባብ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ ይችሉ ዘንድ ጠቃሚ መረጃ ከጥናቱ ሊገኝ ይችላል በሚል

ታሳቢነት ነው። በዚህ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ያሉት የ10ኛ ፣የ11ኛና የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች በጥናቱ ያልተመረጠበት ምክንያት በከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተና ላይ አማርኛን ስለማይፈተኑ አስፈላጊውን መረጃ በማግኘቱ ሂደት ላይ አጥኚዋ እምነት በማጣቷ ነው።

ይህም በያለዉ (1998፡157) "ተመራማሪዉ ከሁሉ አስቀድሞ ተጠኚዎቹን ማወቅ፤ ማለትም ተጠኚዎቹ ተመራማሪዉ የሚፈልገዉን መረጃ ሊሰጡት ይችላሉ? መረጃዉ አላቸዉ? ሁሉንም የሚጠይቃቸዉን ጥያቄዎች አስመልክቶ እዉቀቱና በቂ የህይወት ገጠመኙ አላቸዉ? ተገቢና ትክክለኛ ምላሽ ሊሰጡት ይችላሉ? የመሰሰሉትን ጥያቄዎች መመለስ ከቻለ ተጠኚዎቹ መረጃ አላቸዉ ማለት ነዉ" ያለዉን መሰረት በማድረግ ነዉ። ቀጥሎ የሚኖረው ተግባር ተጠኝ ተማሪዎችን መለየት ነው። የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት 318 ናቸው። ከነዚህም ውስጥ ወንድ 173 ሴት 145 ድምር 318 ሲሆኑ ከስድስት ክፍል የተመረጡ ናቸው። እያንዳንዱ ክፍል 53 ተማሪዎች አሉት።

### 3.1.3. የተጠኚ ተማሪዎች አመራረጥ

በጅማ ዞን በአጋሮ ወረዳ በጅዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በ2016ዓ.ም 9ኛ ክፍል በመማር ላይ ከሚገኙት 318 ተማሪዎች አጥኚዋ ሊያጋጥሟት ከሚችሉት የጊዜ የበጀትና የሰው ሃይል እጥረት አንፃር ከእያንዳንዱ ክፍል ማለትም ከ9ኛክፍል ተማሪዎችን በናሙና ቀመር $173x^{40}/100$ = 70 ተማሪዎችን፤ 70 ወንዶችና ሴት ተማሪዎችን፣ ከ145 ተማሪዎች 145X40/100 = 58፤ ተማሪዎች በጠቅላላው ከ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን በድምሩ 70 +58= 128 ተማሪዎች 70 ወንድ ተማሪዎችና 58 ሴት ተማሪዎች በየማነህ ፎርሙላ በመጠቀም ከ9ኛ ክፍል 70 ወንድ ተማሪዎች የጠቅላላዉን (173) ተማሪዎች 40%፤ ከ9ኛ ክፍል 58 ሴት ተማሪዎች የጠቅላላዉን (145) ተማሪዎች 40% የሚይዙ ስለሆኑ አማካይ ዉክልና እንደሚኖራቸዉ በመተማመን በናሙናነት መመረጥ እንደሚገባቸዉ በመወሰን በቁጥር 128 የሆኑ ተማሪዎች ከሁሉም ክፍሎች በዕጣ ናሙና ዘዴ በመጠቀም ተመርጠዋል። የተሳታፊዎቹ ማንነትና ያሉበት ክፍልም ተለይቶ መረጃዉን እንዲሰጡ ተደርገዋል።

አጥኚዋ በዕጣ 128 ተማሪዎችን የመረጠች ሲሆን ለናሙና በዕጣ ዘዴን የተጠቀመችበት ምክንያት መረጃው በሚሰበሰብባቸው የመማሪያ ክፍሎች መጠይቅ በማሰራጨት ጥናቱ በሚመለከተው አካል ውስጥ ያለው እያንዳንዱ አባል በእኩል ደረጃ የመምረጥ ዕድል ስለሚሰጥ ወይም በአንድ ጥናት ሊካተቱ የሚችሉባቸው ናሙናዎች ብዙሃንን እንደሚወክሉ በማድረግ በከፍተኛ ደረጃ ስለሚጠቅምነው።

ያለው እንዳወቀ (1998 ፡123) በዕድል ሰጪ የናሙና ዘዴ እያንዳንዱ የጥናቱ አካላይ አባል ለጥናቱ ናሙና ሆኖ ለመመረጥ የተወሰነ ዕድል አለው፡፡ በርግጥ ዕድሉ ይህን ያህል ነው ብሎ መናገር አይቻልም፡፡ ተመራማሪው ለመጠቀም እንደሚወስነውና እንደሚያስፈልገው የናሙና ሂደት ይለያያል፡፡ በዕድል ሰጪ የናሙና ዘዴ ተመራማሪው ሳይንሳዊ ዘዴንና ሎጂክ መሰረት አደርጎ የጥናቱን አካላይ ባህሪይ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን ይመርጣል፡ ፡ በዚህ ወቅት የግሉን የግምገማ ሂደት አይከተልም፡፡

ጥናቱ ከ9ኛ ክፍል ተማሪዎችበ 57፤ ወንዶችና በ53 ሴት ተማሪዎች ላይ ተካሂዷል፡፡ ምክንያቱም ከተመረጡት 70 ወንድ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች፤ ውስጥ 8 ተማሪዎች በተሰጠዉ መመሪያ መሰረት መጠይቁን ባለመሙላታቸዉ በአሰራር የተበላሸ ተብሎ የተያዘ ሲሆን እንዲሁም 5 ወንድ ተማሪዎች መጠይቁ በተሞላ እለት ባለመገኘታቸው ከ70 ወንድ 13ቱ ከጥናቱ ውጭ በመሆናቸው ምክንያት እንዲሁም ከ58 ሴት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ 3 ሴት ተማሪዎች መጠይቁን በትክክለኛዉ መመሪያ መሰረት ባለመሙላታቸዉ በአሰራር በተበላሸዉ ዉስጥ ተይዞዋል፡፡ በተጨማሪም መጠይቁ በተሞላበት እለት 2 ተማሪዎች ሊገኙ ባለመቻላቸዉ ከ58 ሴት ተማሪዎች ዉስጥ 5 ተማሪዎች ከጥናቱ ዉጪ ሆነዉ በጠቅላላዉ በ110 ተማሪዎች ብቻ ጥናቱ ሊካሄድ ችሏል፡፡

## 3.2. የመረጃ መሰብሰቢያዎች

አጥኚዋ የጥናቱን መሰረተ አነሳስ ከግንዘቤ ዉስጥ በማስገባት ጥናቱን ከግብ ለማድረስ የመረጠችው የመረጃ መሰብሰቢያ አንደኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭ ተማሪዎች ሲሆኑ ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ዋቢናቸው ዋቢዎችን መሰረት በማድረግመ የተነሳሽነትን መጠንና ዓይነት ሊያሳዩ የሚችሉ የጽሑፍ መጠይቅ ምልክታና የተጠኚ ተማሪዎችን የትምህርት ውጤት ያስገኛል ብላ ያመነችበትን የአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ፈተናን ነው፡፡

### 3.2.1. የጽሑፍ መጠይቅ

መጠይቁ ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋን የንባብ ክህል ለመማር ተነሳሽነት ያላቸው ወይም የሌላቸው መሆኑን ለመለየት ለመረጃ መሰብሰቢያነት ተመርጧል፡፡

ሌላው የጽሑፍ መጠይቅ ለጥናቱ የተመረጠበት ምክንያት መጠይቁ ከሌሎች መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ጋር ሲነፃፀር ጊዜን ጉልበትንና ገንዘብን ስለሚቆጥብና የመላሾችን ማንነት ስለማይገልጽ መላሾች በነፃነት የሚሰማቸውን መልስ ለመስጠት ስለሚያስችል ጠቃሚ መረጃን ለማግኘት ከመርዳቱም ባሻገር በአንድ ጥናት ዉስጥ ለሚካተቱት ተጠኚዎች የሚዘጋጅ የጽሑፍ መጠይቅ የሚይዛቸዉ ጥያቄዎች አንድ ዓይነት በመሆናቸዉ ከጥያቄ

አቀራረብ ልዩነት የተነሳ የሀሳብ ልዩነት እንዳይፈጠር ማድረጉንም ያለዉ (1998) አበክረዉ ይገልጻሉ፡፡

የጽሑፍ መጠይቁ ሲዘጋጅ ከርዕስ ጉዳዩ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸውን ጥያቄዎች በማዘጋጀት ጥናቱ በሚካሄድበት ቦታ በመገኘት ተጠኚዎች (ተማሪዎች) መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጎዋል፡፡ የመጠይቁም ዓይነት ዝግ ጥያቄዎችን የያዘ ነዉ፡፡

በጠቅላላዉ 41 አርባ አንድ ጥያቄዎችን ያካተተዉ የመጠይቁ ዝግጅት ጋርድነር (2004) ከተጠቀመባቸዉ ጥያቄዎች ለጥናቱ በሚያመች ሁኔታ በማሻሻል ወደ አማርኛ የተተረጎሙ ናቸዉ፡፡

የመጠይቆቹ አቀራረብ የጥናቱን መሰረታዊ አነሳስ የተከተሉ ጉዳዮችን ማለትም አስራ አራት ዉስጣዊ ተነሳሽነትን ፤ አስር ሁለት ዉጫዊ ተነሳሽነትን ፤ ዘጠኝ ዉህዳዊ ተነሳሽነትንና ስድስት ጥቅማ ጥቅማዊ የተነሳሽነት ዓይነቶችን እንዲለኩ ተደርገዉ የተቀነባበሩ ናቸዉ፡፡

በዚሁ መሰረት ዉስጣዊ ተነሳሽነትን የሚያመለክቱት ጥያቄ ቁጥሮች 1ኛ፣ 5ኛ፣ 11ኛ 15ኛ፣ 16ኛ፣ 21ኛ፣ 22ኛ፣ 25ኛ፣ 28ኛ፣ 30ኛ፣ 32ኛ፣ 34ኛ፣ 35ኛ፣ 40ኛ ጥያቄዎች ሲሆኑ፤ዉጫዊ ተነሳሽነትን የሚያመለክቱ ጥያቄ ቁጥሮች ደግሞ 2ኛ፣ 6ኛ፣ 8ኛ፣ 12ኛ፣ 18ኛ፣ 19ኛ፣ 20ኛ፣ 24ኛ፣ 26ኛ፣ 31ኛ፣ 36ኛ፣ 39ኛ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ እንደዚሁ ዉህዳዊ ተነሳሽነትን የሚያመለክቱ ጥያቄ ቁጥሮች 3ኛ፣ 4ኛ፣ 9ኛ፣ 13ኛ፣ 17ኛ፣ 27ኛ፣ 29ኛ፣ 33ኛ፣ 41ኛ ጥያቄ ቁጥሮች ሲሆኑ ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነትን የሚያመለክቱት ጥያቄ ቁጥሮችደግሞ 7ኛ፣ 10ኛ፣ 14ኛ፣ 23ኛ፣ 37ኛ፣ 38ኛ ጥያቄዎች በመሆን የቀረቡ ናቸዉ፡፡ የጥያቄዎቹ አቀራረብ ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ ሆኖ:- በጣም እስማማለሁ 5 እስማማለሁ 4 በመጠኑ እስማማለሁ 3 አልስማማም 2 በጣም አልስማማም 1 ሆነዉ በሰንጠረዥ ተዘጋጅተዋል፡፡

ጥያቄዎቹ በሰንጠረዥ እንዲቀርቡና ባለ አምስት የመልስ መወሰኛ አማራጭ እንዲሆን የተፈለገዉ ተማሪዎቹ በአሞላሉ ሂደት ተሰላችተዉ አሞላሉን እንዳያበላሹት በመስጋትነዉ፡፡

መጠይቆቹ ወደ ትግበራ ከመግባታቸዉ አስቀድሞ በጥናቱ አማካሪዎች ታይተዋል፡፡ ከዚያም በእጣ የናሙና ዘዴ የተመረጡትን ተማሪዎች በመለየት

በጅዳ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መረጃዉን ለማሰባሰብ ከርዕሳነ መምህራኑ ከተማሪዎችና ከሚመለከታቸዉ አካሎች ጋር ስምምነት ላይ ከተደረሰ በኋላ በዚህ 2ኛ ደረጃ ትምህርት

ቤት በአንድ የላቦራቶሪ ክፍልና በአንድ የተማሪዎች የቱቶሪያል ትምህርት መስጫ ክፍል ዉስጥ ገብተዉ በመጠይቁ ላይ የቅደም ተከተላቸዉን መሰረት የጠበቀ መለያ ኮድ ተሰጥቶአቸዉ ወደ ስራዉ ተገብቶዋል፡፡

ተሳታፊ ተማሪዎች የየግለቸዉን ስሜት ፣ ባህሪያት ፣ አመለካከትና ዉሳኔን ይወክላሉ ያሉዋቸዉን አማራጮች እንዲመርጡ በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህርና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምህራን በአፋን ኦሮሞ እና በአማርኛ ቋንቋዎች ተጨማሪ ማብራሪያ ከተሰጣቸዉ በኂላ ተማሪዎቹ የየግላቸዉን ትክክለኛ ስሜትና አመለካካት ያመላክቱ ዘንድ ብሎም በመጠይቁ አሞላል ሂደት ላይ ሀሳብ እንዳይለዋወጡ ከፍተኛ ጥንቃቄ ተደርጎ መጠይቁ በመልካም ስነምግባር ተሞልቶ ተጠናቆዋል፡፡

### 3.2.2. የችሎታ መለኪያ ፈተና (Achievement Test)

ዋናው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የችሎታ መለኪያ ፈተና ነው፡፡ ትምህርትና ፈተና የማይነጣጠሉ ይልቁንም ጎን ለጎን የሚሄዱ ጉዳዮች በመሆናቸው የጠበቀ ቁርኝት አላቸው፡፡

ፈተና ማለት የተወሰኑ ጥያቄዎች ተዘጋጅተዉ ወጥነት ባለዉ መንገድ የተፈታኞችን አዕምሮአዊ ወይም ስነ ባህሪያዊ ሁኔታ አስመልክቶ መረጃ ለመሰብሰብ የሚረዳ መለኪያ ነዉ፡፡ እዚህ ላይ ወጥነት ሲባል ፈተናዉ ለጥናቱ ተሳታፊዎች የሚሰጠዉ በተመሳሳይ ሁኔታ ማለትም በተመሳሳይ የጊዜ ገደብ የአፈታተንና የአስተራረም መንገድ ፣ ተመሳሳይ የመልስ አሰጣጥ መልክና መመሪያ እና ከተቻለም በተመሳሳይ ፈታኝ ወይም ተቀራራቢ የአፈታተን ብቃት ባለቸዉ ሰዎች የሚካሄድ መሆኑን ለማመልከት ነዉ፡፡ያለዉ (1998፡194)

Bachman (2010፤26-27) ፈተና መፈተን ያስፈለገበት ዋና ዓላማው መረጃን ሰብስቦ ውሳኔ ለመስጠት ነው፡፡ መረጃውም ተማሪዎች ለንባብ ትምህርት ያላቸው ተነሳሽነት፣ የንባብ ፍላጎት፣ ስለ ንባብ ያላቸው አስተያየት፣ ስለ ስሜታቸውና የሚያነቡትን ንባብ መረዳት መቻል ላይ አጠቃላይ የሆነ አመለካከት ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ አንፃር ሲታይ የፈተናው መሰጠት የተፈለገው ለራሱ ለመምህሩ ቢሆን እንኳን ንባብን ስለማስተማር ስልቱና ችሎታው መረጃን ለማግኘት ሊሆን ያስችላል፡፡ በመሆኑም ፈተና ውሳኔዎች መቼና እንዴት መተግበር እንዳለባቸው ለመወሰን ያስችላል፡፡ አክለውም Bachman (2001'1) አጠቃላይ የፈተናን ምንነት ሲገልጹ "የሰው ልጅ በገሃዱ ዓለም ላይ ፈተናን የሚጠቀመው አንድን ነገር ለመወሰን በቂ መረጃን ስለ ሚያስገኝለት ነው " ይላሉ፡፡

አጥኚዋ የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት ለማግኘት ፈተናን በመረጃ መሰብሰቢያነት መጠቀም የፈለገችበት ምክንያት ከተማሪዎች ውጤት ማጠራቀሚያ

ላይ ከሚገኘው ውጤት የተሻለ ትክክለኛነትና አስተማማኝነት ሊኖረው ይችላል ብላ ስላመነችበት ነው፡፡

የፈተናው አዘገጃጀት እንደሚከተለው ነው፡፡ ይኸውም አጥኚዉ ከፈተናው ዝግጅት አስቀድሞ በ9ኛክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ከሚገኙት ምንባብዎች አንዱን ለይታለች፡፡ ቀጥሎ በትምህርት ቤቱ በተለመዱት የፈተና አወጣጥ መሰረት ምንባቡን መሰረት ያደረገ ፈተና በአጥኝዋ ተዘጋጅቷል፡፡

የፈተናው ጥያቄዎች አወጣጥ የአንብቦ መረዳት ፈተና ባህሪያትን ማሟላት አለማሟላታቸው ለማረጋገጫ በትምህርት ቤቱ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምህራን ተገምግሞዋል፤ በጥናቱ አማካሪም ታይቶ የማስተካከያ ሀሳብ ተሰጥቶበት እንደገና ተስተካክሏል ፡፡

በዚሁ መሰረት ቀደም ሲል ለተጠኚዎቹ በተገለፀዉ የመገናኛ ቀጠሮ እለት ተጠኚዎቹ ተገኝተዉ ቀደም ሲል በተሞላላቸዉ የፅሁፍ መጠይቅ ላይ የተሞላዉን የኮድ ቁጥር በፈተናዉ ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ በጥንቃቄ ተሞልቶላቸዉ በቅደም ተከተላቸዉ ከታደለ በሁዋላ የፈተናዉ ስራ ተጠናቆ መረጃዉ ሊሰበሰብ ችሏል፡፡

### 3.2.3.ምልከታ

ለጥናቱ ከተመረጡ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መሀከል አንዱ ምልከታ ነው፡፡ምልከታው የተካሄደው ውስን የምልከታ ስልት በመከተል ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት የትምህርት ሂደቱ በክፍል ውስጥ በሚከናወንበት ጊዜ አስፈላጊ በሆኑ ዋና ዋና ነጥቦች ላይ በማተኮር በአጭር ጊዜና በቀላል መንገድ ለማከናወን ስለሚያስችል ነው፡፡

አላማውም በክፍል ውስጥ በአካል በመገኘት የንባብ ክሂል ትምህርት ላይ የተማሪዎች ተነሳሽነት ምንእንደሚመስል መፈተሽ ነው፡፡ምልከታው በጅዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በስድስት የዘጠነኛ ክፍል ምድብ ውስጥ ተካሂዷል፡፡ለምልከታው ያገለገለው ቅፅ የተዘጋጀው በጥናቱ አማካሪ አስተያየት ተሰቶበት ነው፡፡በመሆኑም አጥኝዋ ለምልከታ የወጣውን የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በማድረግ በስድስቱም ተጠኝ ምድብ መምህሩ የንባብ ትምህርት በሚያስተርበት ክፍል ለሁለት ሁለት ጊዜያት ምልከታን በማካሄድ የተማሪዎችን የንባብ ተነሳሽነት በመማር ማስተማሩ ሂደት ምን እንደሚመስል ፣የተማሪዎቹ ተሳትፎ ምን ያህልእንደሆነ እና በሂደቱ ውስጥ ምን ምን ችግሮች እንደተከሰቱ ከተቀመጠው መስፈርት እና ከትኩረቱ አንፃር ተፈትሾ ውጤቱ በስታቲስቲካዊ ስልት በገለፃ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

ከቀን 15/8/2016 እስከ 3/9/2016 ዓ.ም በእያንዳዱ ዙር ለሰላሳ አምስት ደቂቃ ምልከታው ተከናውኗል፡፡ይህም ተማሪዎቹ ለንባብ ትምህርት ያላቸው ተነሳሽነት ከንባብ በፊት ፣በንባብ ጊዜ እና ድህረ ንባብ ሂደት ላይ ያላቸውን ተነሳሽነት የመከታተያ ቅፅ ተዘጋጅቷል ፡፡ የመከታተያ ቅፁም ተከናውኗል ፣በከፊል ተከናውኗል እና አልተከናወነም የሚል አማራጭ ደረጃዎችን በያዙ በሰንጠረዝ ውስጥ ምልከታ ተደርጎበታል የእያንዳንዱ ምልከታ ሂደት በአይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ተገልጿል፡

## 3.3. የመረጃ አተናተን ዘዴ

ከተጠኚዎች የተሰባሰቡት መረጃዎች መልሶች ተጠይቃዊ በሆነ መንገድ በትክክል መሞላታቸው ከተጣራ በኋላ ለትንታኔ እንዲያመች ኮድ ተደርጎዋል፡፡ ከዚያም በውጤት መመዝገቢያው ሠንጠረዥ (ኮድ ሽት) በኮምፒውተር ላይ ሰፍሯል፡፡ በመጨረሻም ወደ ትንታኔ ሳይገባ በተሞላው መረጃ ላይ የመጨረሻው ማጣራት ተካሂዶ ወደ ትንታኔ ተገብቶዋል፡፡

የጥናቱን ተሳታፊ ተማሪዎች የንባብ ተነሳሽነት ለማወቅ በተቀመጡት የመነሻ ጥያቄዎች መሠረት በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎችን (በSPSS version 24) ገላጭ ስታስቲክስን ማለትም የተማሪዎችን አማካይ ውጤት፣ መደበኛ ልይይትና በመቶኛ ደረጃ ምን እንደሚመስሉ ለማብራራት ተግባር ላይ ውሏል፡፡

ተዛምዶን (Correlation) አስመልክቶ በሁለት ተለዋዋጮች መካከል ዝምድና መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ የፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ስራ ላይ ውሏል፡፡

# ምዕራፍ አራት
# የመረጃ ትንተናና ማብራሪያ

## 4.1 የመረጃ ትንተና

በቀደምት የተለያዩ የጥናቱ ክፍሎች ለመግለጽ እንደተሞከረው የዚህ ጥናት መሰረታዊ ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ክሂል ትምህርት ተነሳሽነት ከትምህርት ውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ መርምሮ ውጤቱን ለማየት ነው፡፡ በዚህ መሰረት በ41 የጽሑፍ መጠይቅ ጥያቄዎች የተሰበሰበው መረጃና በ45 የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ፈተና እንዲሁም 10 መስፈርት በያዘ የምልከታ ቅፅ መሰረት የተገኘው ውጤት በምዕራፍ አንድ ላይ የሰፈሩትን የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች እንደሚከተለው ለመመለስ ተችሏል፡፡

### 4.1.1. የጥናቱ ተሳታፊዎች አጠቃላይ መረጃ

ሰንጠረዥ ሐ፡

| ፆታ * ትምህርትቤት Crosstabulation | | | |
|---|---|---|---|
| | | | ትምህርትቤት |
| | | | ጅዳ |
| ፆታ | ሴት | ብዛት | 53 |
| | | ፐርሰንት | 48.2% |
| | ወንድ | ብዛት | 57 |
| | | ፐርሰንት | 51.8% |
| ድምር | | ብዛትt | 110 |
| | | ፐርሰንት | 100.0% |

በሰንጠረዥ 1፡ የተቀመጠው የጥናቱ ተሳታፊዎች አጠቃላይ መረጃ እንደሚያሳየው ከፆታ አንጻር ሲታይ 53 (48.2%)ሴት ተማሪዎች የተሳተፉ ሲሆን፣ ወንዶች ደግሞ 57 (51.8%) ወንዶች ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

### 4.1.2. የፈተና ውጤት

ሰንጠረዥ መ

| ፆታ | አማካይ | N | መ. ል(S. D) |
|---|---|---|---|
| ሴት | 53.0189 | 53 | 10.91663 |
| ወንድ | 54.0526 | 57 | 10.44103 |
| ድምር | 53.5545 | 110 | 10.63626 |

ከላይ በሰንጠረዠ ሁለት እንደተመለከተው በአጠቃላይ በወንዶች እና በሴቶች ተማሪዎች አጠቃላይ የፈተና ወጤት አንፃር ሲታይ የወንዶች ተማሪዎች የፈተና አማካይ ዉጤት 54.0526 መደበኛ ልይይት 10.44103 የሴቶች ተማሪዎች አማካይ የፈተና ዉጤት 53.0189 መደበኛ ልይይት 10.91663 ነው፡፡

### 4.1.3. የተማሪዎችን የንባብ ተነሳሽነት የሚያሳይ ገላጭ እስታትስትክስ

ሰንጠረዥ ሠ

| | | አማካይ | መደበኛ ልይይት | ልዩነት |
|---|---|---|---|---|
| ውስጣዊ | | 3.4534 | .51869 | .269 |
| ውጫዊ | | 3.7058 | .61702 | .381 |
| ውህዳዊ | | 4.3182 | .63667 | .405 |
| ጥቅማ ጥቅማዊ | | 3.5195 | .70829 | .502 |

በሰንጠረዥ ሠ እነደተመለከተው የተማሪዎች አማርኛ የማንበብ ተነሳሽነት ውጤት በእያንዳንዱ የተነሳሽነት አይነቶች ሲታይ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

በአጠቃላይ የተማሪዎቹ ውስጣዊ የንባብ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት 3.4534 እና የመደበኛ ልይይት 0.51869 ውጫዊ የንባብ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት 3.7058 እና መደበኛ ልይይት 0.617 ዉህዳዊ የንባብ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት 4.3182 እና የመደበኛ ልይይት 0.6366 እና ጥቅማጥቅማዊ የንባብ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት 3.5195 እና መደበኛ ልይይት 0.70829 ሆኖዋል፡፡

ከላይ በተገለፀዉ መሰረት ከአራቱ የተነሳሽነት አይነቶች ተማሪዎቹ የተሻለ የተነሳሽነት ውጤት ያሳዩት በውህዳዊ የተነሳሽነት አይነት ሲሆን አማካይ ውጤቱ 4.3182 ነው በቀጣይነት የተማሪዎቹ ውጤት በጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት 3.5195 በማሳየቱ ከውህዳዊ ተነሳሽነት ቀጥሎ የተማሪዎቹ ተነሳሽነት ጎልቶ የሚታየው በጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ላይ መሆኑ ተስተውሎዋል፡፡

ይህም አፋን ኦሮሞ አፈ-ፈት የሆኑት የጅዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የንባብ ትምርታቸውን የሚከታተሉት በአብዛኛው ከውስጣዊ ተነሳሽነት ይልቅ በውህዳዊ ተነሳሽነት ደረጃ እንደሆነና በደረጃ ሲቀጥልም በጥቅማጥቅማዊ ተነሳሽነት ደረጃ መነሳሳት እንደሚታይባቸው አመላካች ነው፡፡ ይህም ማለት የውህዳዊና የጥቅማጥቅማዊ ተነሳሽነት አላማ ያላቸው ተማሪዎች በንባብ ትምህርታቸው ውጤታማ መሆናቸውን ያመላከተ ጥናት መሆኑን ያሳያል፡፡

### 4.1.4. የተማሪዎች የንባብ ተነሳሽነት እና የውጤት ተዛምዶ

ሰንጠረዥ ሯ

| | | የፈተና ውጤት | ውስጣዊ | ውጫዊ | ውህዳዊ | ጥቅማጥቅማዊ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የፈተና ውጤት | የፒርሰን ተዛምዶ | 1 | | | | |
| | የፒ ዋጋ | | | | | |
| ውስጣዊ | የፒርሰን ተዛምዶ | -.050 | 1 | | | |
| | የፒ ዋጋ | .607 | | | | |
| ውጫዊ | የፒርሰን ተዛምዶ | -.186 | .616** | 1 | | |
| | የፒ ዋጋ | .051 | .000 | | | |
| ውህዳዊ | የፒርሰን ተዛምዶ | -.089 | .260** | .372** | 1 | |
| | የፒ ዋጋ | .354 | .006 | .000 | | |
| ጥቅማጥቅማዊ | የፒርሰን ተዛምዶ | -.250** | .727** | .645** | .307** | 1 |
| | የፒ ዋጋ | .008 | .000 | .000 | .001 | |
| **. Correlation is significant at the 0.01 level (2-tailed). | | | | | | |

**.የሚያመለክተው በ 0.01 በጉልህነት ደረጃ ዝምድናው ተጨባጭ መሆኑን ነው
የተማሪዎች ብዛት 110 ነው

በሰንጠረዠ 4 እንደተቀመጠው የተማሪዎች የንባብ ተነሳሽነት እና የፈተና ውጤት ተዛምዶ ደረጃ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ተቀምጧል በተነሳሽነት እና ለትምህርት ውጤት መካከል ዝምድና መኖሩ የሚረጋገጠው ውጤት በ -1 እና በ 1 መካከል ሲመጣ ነው፡፡ ከዚህም ውጪ የፒ ዋጋ ከ 0.05 በታች ከሆነ ተለዋዋጮቹ ዝምድና አላቸው ይባላል፡፡ ከፒ ዋጋ በላይ ከሆነ ግን ዝምድና አይኖራቸውም በዚሁ መሰረት የእያንዳንዱ የተነሳሽነት አይነት እና የውጤት ተዛምዶ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

**አንደኛ** ውስጣዊ የንባብ ተነሳሽነት እና የትምህርት ውጤት በ ፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ሲታይ ዝምድና የላቸውም፤ምክንያቱም ውስጣዊ ተነሳሽነት እና የፈተና ውጤት -0.050 ከመሆኑም ሌላ የፒ ዋጋ ከ 0.05 % በላይ ማለትም 0.607 % ስለሆነ ነው፡፡

**ሁለተኛ** ውጫዊ የንባብ ተነሳሽነት እና የትምህርት ውጤት በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ሲታይ ዝምድና የላቸውም፡፡ ምክንያቱም የውጫዊ ተነሳሽነት እና የተማሪዎቹ የፈተና ውጤት -0.186 ከመሆኑም በላይ የፒ ዋጋ 0.051% ስለሆነ ነው፡፡

**ሶስተኛው** የውህዳዊ የንባብ ተነሳሽነት እና የተማሪዎች የፈተና ውጤት በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ሲታይ ዝምድና የላቸውም ምክንያቱም የፒርሰን ተዛምዶ -0.089 ወይም የፒ ዋጋ .354 % ስለሆነ ነው፡፡

**አራተኛው** ጥቅማጥቅማዊ የንባብ ተነሳሽነት እና የተማሪዎቹ የፈተና ውጤት በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ከፍተኛ ግንኙነት (ዝምድና) አላቸው ምክንያቱም የፒርሰን ተዛምዶ ዋጋው -0.25 ወይም የፒ ዋጋ 0.008% በመሆኑ ነው፡፡ይህም ተዛምዶዉ ጉልህ መሆኑን ያመለክታል፡፡

### 4.1.5 ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ

ሰንጠረዥ ሰ

| | | ተከና ዉኗል | % | በከፊልተከ ናዉኗል | % | አልተከ ናወነም | % | ድም |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቁ | ከንባብ በፍት የተማሪ ድርሻ | ቁ | | ቁ | | | | |
| 1 | ሁሉም ተማሪዎች መፅሀፍ መያዝ | | | 6 | 50 | 6 | 50 | 100 |
| 2 | ስለምን እንደሚያነዉ መገመት | 1 | 8.33 | 7 | 58.33 | 4 | 33.33 | 99.93 |
| 3 | ከቀደመ እዉቀታቸዉ ጋሪ ርፅሱን ማዛመድ | | | 4 | 33.33 | 8 | 66.6 | 99.93 |
| 4 | የንባቡን አላማ መረዳት | 1 | 8.33 | 5 | 41.6 | 6 | 50 | 99.93 |
| | ለ የንባብን ጊዜ የተማርዎች ደረሻ | | | | | | | |
| 1 | ቅድመምንባብጥያቀዎች ን እያረጋገጡ መሄድ | 1 | 8.33 | 6 | 50 | 5 | 41.6 | 99.93 |
| 2 | ምንባቡን ገታ በማድረግ ጥያቀ መመለስ | | | 6 | 50 | 6 | 50 | 100 |
| 3 | የአዳድስ ቃላት ትርጉም መገመት | 2 | 16.6 | 7 | 58.33 | 3 | 25 | 99.93 |
| 4 | የምንባቡን መልፅክት ማግኘት | 2 | 16.6 | 6 | 50 | 4 | 33.33 | 99.93 |
| ሐ የድህረ ንባብ ጊዜ የተማርዎች ድርሻ | | | | | | | | |
| 1 | የምንባቡንዋና መልፅክት መናገር | 3 | 25 | 5 | 41.6 | 4 | 33.33 | 99.93 |
| 2 | ከምንባቡየወጡጥያቀዎ ችን መመለስ | 3 | 25 | 6 | 50 | 3 | 25 | 100 |

### 4.1.5.1 ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና

የዚህ ጥናት አላማ ተማሪዎች ለንባብ ትምህርት ያላቸው ተነሳሽነት ከውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ነው፡፡በመሆኑም የተማሪዎችን ለንባብ ያላቸውን ተነሳሽነት ለመመዘን እንዲሁም በፅሁፍ መጠይቅ ዘዴ የተሰበሰበውን የንባብ ተነሳሽነት በሚመለከት የተገኘውን መረጃ ለማጠናከር ምልከታ ተካሂዷል ፡፡በጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት ስድስት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ ለሁለት ሁለት ጊዜያት በድምሩ ለአስራሁለት ጊዜያት ምልከታው ተከናውኗል፡፡በተጨማሪም የተለያዩ የምልከታ ነጥቦች እና ተያያዥ ተግባራትን በሰንጠረዥ በመዘርዘር አተገባበራቸውን ሊገልፅ በሚችሉ መልኩ ተከናውነዋል ፣ በከፊል ተከናውነዋል ፣አልተከናወነም የሚሉ አማራጮች ቀርበው ምልከታው ተከናውኗል የመረጃ ትንተናው እንደሚከተለው ቀርቦል፡፡

ከምንባብ በፊት የተማሪ ድርሻ ሁሉም ተማሪዎች መፅሀፍ መያዛቸው በከፊል ተከናውኗል 6 (50%) አልተከናወነም 6 (50%) የሚለውን ያመለክታል፡፡ ስለምነ እንደሚያነቡ መገመት 1 (8.33%) ተከናውኗል ፣7 (58.33%) በከፊል ተከናውኗል፣4 (33.33%)አልተከናወነም ያመለክታል፡፡ከቀደመ እውቀታቸው ጋር ርእሱን ማዛመድ 4 (33.33%) በከፊል ተከናውኗል 8 (66.6%)አልተከናወነም የንባቡን አላማ መረዳት 1 (8.33%) ተከናውኗል 5 (41.6%) በከፊል ተከናውኗል፣6(50%) አልተከናወነም ያመለክታል፡፡

በንባብ ጊዜ የተማሪዎች ድርሻ ቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን እያረጋገጡ መሄድ 1 (8.33%) ተከናውኗል 6(50%) በከፊል ተከናውኗል፣ 5 (41.6%) አልተከናወነም፡፡ ምንባቡን ገታ በማድረግ ጥያቄ መመለስ 6(50%) በከፊል ተከናውኗል ፣6(50%) አልተከናወነም፡፡የአዳዲስ ቃላት ትርጉም መገመት 2(16.6% ) ተከናውኗል ፣7 (58.33%) በከፊል ተከናውኗል፣3 (25%) አልተከናወነም ፡፡የምንባቡን መልክት ማግኘት 2(16.6% ) ተከናውኗል ፣6(50%) በከፊል ተከናውኗል፣4 (33.33%) አልተከናወነም ፡፡

የድህረ ንባብ ጊዜ የተማሪዎች ድርሻ የምንባቡን ዋና መልክት መናገር 3 (25%) ተከናውኗል፣5 (41.6%)በከፊል ተከናውኗል ፣4 (33.33%)አልተከዋወነም፡፡ ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን መመለስ 3 (25%) ተከናውኗል፣7 (58.33%) በከፊል ተከናውኗል፣3 (25%) አልተከናወነም፡፡ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ከምልከታ የተገኘ መረጃ እንደሚያመለክተው ተነሳሽነታቸው መካከለኛ እንደሆነ የሚያሳይ ነው ስለሆነም በፅሁፍ መጠይቅ የተገኘውን መካከለኛ ተነሳሽነት ያረጋገጠ ምልከታ ነው፡፡

## 4.2. የውጤት ማብራሪያ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በሁለተኛ ቋንቋ የንባብ ተነሳሽነትና ውጤት መካከል የሚገኘውን ተዛምዶ የሚመለከት ሲሆን በ41 የጽሑፍ መጠይቅና 45 ጥያቄዎችን ባካተተ የአንብቦ መረዳት ፈተና እንዲሁም በምልከታ በተሰበሰቡ መረጃዎች መነሻነት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ የማንበብ ተነሳሽነት ከፈተና ውጤታቸው ጋር ሲነጻፀር የትኛው የንባብ ተነሳሽነት ዓይነት ከፈተና ውጤት ጋር የጎላ ተዛምዶ እንዳላሳየ፣ የንባብ ተነሳሽነት ዓይነቶች ያላቸው የርስ በርስ ተዛምዶ ምን ዓይነት እነደሆነ ለመለየት በተለያዩ ገላጭ በሆኑና ተንበይ በሆኑ እስታቲስቲኮች ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

በቅደም ተከተል ከተቀመጡት የጥናቱ ጥያቄዎች የምላሽ ቅድሚያ ያገኘው የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ አፈ-ፈት ሆነው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የንባብ ተነሳሽነት እንዳላቸውና እንደሌላቸው ለማረጋገጥ የቀረበው ጥያቄ ነው፡፡

በሰንጠረዥ 4 ላይ እንደታየው በአፋን ኦሮሞ አፈ-ፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ተነሳሽነት ምን ያህል ነው ለሚለው ጥያቄ ከጽሑፍ መጠይቁ የተገኘው የተማሪዎቹ አማርኛን የንባብ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት በደረጃ ቅደም ተከተል የውህዳዊ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት 4.3182 እና መደበኛ ልይይት 0.63667 ፣ የውጫዊ ተነሳሽት አማካይ ውጤት 3.7058 ሲሆን መደበኛ ልይይት 0.61702 ፣ የጥቅማጥቅማዊ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት 3.5195 እና መደበኛ ልይይት .70829 ሲሆን የመጨረሻው የውስጣዊ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት 3.4534 መደበኛ ልይይት -51869 በመሆኑ ከዚሁ በመነሳት የተማሪዎቹ አማርኛን የማንበብ ተነሳሽነት ደረጃ መካከለኛ እንደሆነ መለየት ተችሏል፡፡ በምልከታ የተገኘው ውጤትም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ዳሩ ግን በሰንጠረዥ 4 ላይ የተመለከተው ገላጭ እስታስቲክስ እንደሚያሳየው የተማሪዎቹ አማካይ የአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ተነሳሽነት ውጤት በሰንጠረዥ ሦስት ላይ ከተገለጸው አማካይ የፈተና ውጤት አንጻር ሲታይ የፈተና ውጤቱ አጥጋቢ አይደለም፡፡ ተማሪዎቹ የማንበብ ተነሳሽነት ቢኖራቸውም የፈተና ውጤታቸው ግን አነስተኛ የማለፊያ ነጥብ የሚባለው አከባቢ ይገኛል፡፡

የተማሪዎቹ ተነሳሽነትና የፈተና ውጤታቸው አለመጣጣም ምክንያት የትምህርቱ አቀራረብ ወይም የመማር ማስተማር ሂደቱ ከተማሪዎቹ የማንበብ ተነሳሽነት ጋር የማይጣጣም በመሆኑ ሊሆን ይችላል የሚል ግምት ሊያሰጥ ይችላል፡፡ ይህም በክፍሌ (2002) የተጠቀሱት Devis (1999) የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ራሳቸውን የቻሉ እንዲሆኑና

በዚህም በትምህርቱ ውጤታማ እንዲሆኑ መምህራን ለተማሪዎቻቸው ተከታታይነት ያለው ወቅታዊ የሆነ የተማሪዎችን እምነት አጠናክሮ በደንብ እንዲሰሩ የሚያስችል አዋንታዊ ምላሽ መስጠት እንደሚጠበቅባቸው እንዲሁም በጣም ቀላል  በጣምም ከባድ ያልሆኑ ተግባራትን በመስጠት ተማሪዎች  ስኬታማ የሚሆኑበቸውን አጋጣሚዎች ማመቻቸት ከሚቀርቡላቸው  የትምህርት መሳሪያዎች ውስጥ የራሳቸውን ግላዊ ግንዛቤ የሚያንፀባርቁ ትርጉሞችን እንዲፈልጉ ማድረግ፣ በራሳቸው የሚተማመኑ ፣ዋጋ ያላቸው ጠቃሚ የትምህርት ማህበረሰብ አባላት መሆናቸው እንዲሰማቸው  ሞራላቸውን መጠበቅና ውስጣዊ ተነሳሽነታቸውን ከፍ ማድረግ እንዳለባቸው ከገለጹት ሃሳብ ጋር የሚስማማ ይመስላል፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ Ellis (1995) የተማሪዎች የመማር ተነሳሽነት ከፍተኛ ሆኖ የትምህርት ውጤት ዝቅተኛ መሆን ዝቅተኛ ተነሳሽነት ዝቅተኛ ውጤትን፣ ከፍተኛ ውጤት ደግሞ መልሶ ከፍተኛ ተነሳሽነት እንደሚያስከትል በሚል ከደረሱበት ድምዳሜ ጋር ይቃረናል፡፡ አንደ ኤሊስ ድምዳሜ ቢሆን ኖሮ በዚህ ጥናት ሂደት ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የማንበብ ከፍተኛ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት ትምህርት ፈተና አነስተኛ ውጤት ማስመዝገብ አልነበረባቸውም ነበር፡፡

የጥናቱን 2ኛ ጥያቄ በማስመልከት የተማሪዎቹ የንባብ ትምህርት ተነሳሽነት ከአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ ምን ይመስላል?  ለሚለው ደግሞ በሰንጠረዥ 5 እንደተመለከተው በተደረገው ትንተና በውስጣዊ፣ በውጫዊና በውህዳዊ ተነሳሽነቶችና በፈተና ውጤታቸው መካከል ተዛምዶ አልታየም፡፡ በሌላ መልኩ አንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት ከተዘረዘሩት የተማሪዎች የመማር ተነሰሽነት ዓይነቶች መካከል ከጥቅማጥቅማዊ ተነሳሽነት ጋር ብቻ ተጨባጭ ተዛምዶ አሳይቷል ይህም የሚያሳየው ከጥቅማጥቅማዊ ተነሳሽናት ውጪ ባሉት የውስጣዊ የውጫዊና የውህዳዊ ተነሳሽነት አይነቶች የተማሪዎቹ መነሳሳትና የውጤታቸው አለመዛመድ ችግር መኖሩን ነው፡፡ ከዚህም የምንረዳው በተማሪዎቹ ተነሳሽነት በትምህርት ውጤታቸው መካከል ተዛምዶ አለመኖሩን ነው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ መደምደሚያ እና መፍትሔ

## 5.1 ማጠቃለያ

በቀዳሚዎቹ ምዕራፎች ለማየት እንደተሞከረው የጥናቱ መሰረታዊ ዓላማ የአፋን ኦሮሞ አፊ- ፊት የሆኑ የጅዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች የንባብ ክህል ተነሳሽነትና የትምህርት ውጤት ተዛምዶን መመርመር ነው፡፡

በዚሁ መሰረት በጥናቱ ሂደት መልስ እንዲያገኙ  የቀረቡት ጥያቄዎች

ሀ.  ተማሪዎቹ ለንባብ ክሂል ያላቸው ተነሳሽነት  ምን ያህል ነዉ?
ለ. በየትኛው የተነሳሽነት አይነት ነው የተሻለ መነሳሳት ያሳዩት?
ሐ.ተማሪዎቹ ለንባብ ክሂል ትምህርት ያላቸውን ተነሳሽነት ከአንብቦ መረዳት ፈተና
    ውጤታቸው ጋር ያለው ዝምድና ምን ያህል ነው?

ከላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች  መልስ ለማስገኘት ይቻል ዘንድ የፅሁፍ መጠይቅና ፈተና ለመረጃ መሰብሰቢያነት ተመርጠዉ ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ በእጣ የናሙና ዘዴ የተመረጡት 110 የጅዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ2016 ዓ.ም የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች  የአፋን ኦሮሞ አፊ-ፊት የጥናቱ ተሳታፊዎች ናቸው፡፡አንደኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭ የሆኑት ተማሪዎች ሲሆኑ ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭ ደግሞ ዋቢ ነው፡፡ዋቢን መሰረት መሰረት በማድረግ ለመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በመሆን ያገለገለው የጽሑፍ መጠይቅ፣ ምልከታ እና የአንብቦ መረዳት ትምህርት ፈተና ነው፡፡ አራት ዓይነት የንባብ ተነሳሽነት ዓይነቶችን ለመለካት  የቀረበት በጽሑፍ መጠይቁ ውስጥ የተካተቱት 41 ጥያቄዎች በተለያዩ ጊዜያት በመስኩ ልዩ ልዩ ምርምሮችን ሲያካሄዱ የነበሩት ጋርድኔር (2004) ከአዘጋጁት የጽሑፍ መጠይቅ በማውጣጣት ለምርምሩ በሚያመች ሁኔታ ወደ አማርኛ አሻሻሎ በመተርጎም ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ አስር መስፈርትን የያዙ የምልከታ ቅፅን በማዘጋጀት ምልከታ ተካሂዷል፡፡

የአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት  ፈተናውም በአማካሪዎችና በአማርኛ ቋንቋ መምህራን ማስተካካያ ተደርጎባቸው የተማሪዎቹን የአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በጽሑፍ መጠይቁ በምልከታውና በፈተናው የተሰበሰቡት መረጃዎች የተለያዩ ገላጭ እስቲስቲካዊ ዘዴዎችን በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡

የጥናቱ ትንተና ውጤት እንዳመለከተው አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የአፋን ኦሮሞ አፊ-ፊት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚቀርብላቸው የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት ውስጣዊ፣ ውጫዊ ና ውህዳዊ ተነሳሽነትን መሰረት ያደረገ ቢሆን የተሻለ ውጤት ሊያስመዘግቡ እንደሚችሉ ያመላከተ ነው፡፡ በጥቅማ ጥቅማዊ የመማር ተነሳሽነት በኩል ያለው ውጤት ተዛምዶ መካከል መጠነኛ ልዩነት በመፍጠሩ ውጤቱ በወረደበት በበለጠ ለማሻሻል መበርታት በእጅጉ ጠቃሚ ነው፡፡ የትምህርቱ አሰጣጥ ሂደት በግድ የለሽነት በተመለመደው የመማር ማስተማር አካሄድ የሚቀጥል ከሆነ ግን የተማሪዎቹን የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት ውጤት በቀጣይነት ሊጎዳ እንደሚችል ከጥናቱ ውጤት መገመት እንደሚቻል አጥኚዋ ታምናለች፡፡

## 5.2 መደምደሚያ

ቀደም ሲል በተገለፀዉ የጥናቱ ዉጤት እና ማብራርያ መሰረት እንደሚከተለዉ መደምደሚያ ላይ ተደርሷል፡፡

### 1.ተማሪዎች ለንባብ ክህል ያላቸዉ ተነሳሽነት ምን ያህል ነው

የተማሪዎች የንባብ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት በውሳጣዊ ተነሳሽነት 3.4534፣ መደበኛ ልይይት 0.51869፣ በውጫዊ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት 3.7058 መደበኛ ልይይት 0.617 በውህዳዊ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት 4.3182 መደበኛ ልይይት 0.6366 ሲሆን በጥቅማጥቅማዊ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት 3.5195 እና መደበኛ ልይይት 0.70829 ሲሆን ይህም በአብዛኛው የተማሪዎቹ የተነሳሽነት መጠን መካከለኛ ደረጃ ላይ እንደሆነ ያሳያል፡፡

### 2.ተማሪዎች ለንባብ ያላቸዉ ተነሳሽነት ከፈተና ውጤት ጋር ያለው ተዛምዶ

በአጠቃላይ ሲታይ የንባብ ተነሳሽነት ከአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት ጋር ያለው ተዛምዶ ዝቅተኛ፣ ተቃርኖ እና ተጨባጭ ያልሆነ ነው፡፡ በተጨማሪም የንባብን ተነሳሽነት ዓይነቶች ከአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት ጋር ያላቸው ተዛምዶ ሲታይ ከጥቅማጥቅማዊ ተነሳሽነት ጋር ብቻ ተጨባጭ ተዛምዶ ያለው ሲሆን፣ ከውስጣዊ፣ ውጫዊና ውህዳዊ ተነሳሽነት ጋር ግን ተጨባጭ ተዛምዶ አለመኖሩን ያሳያል፡፡ ከጥቅማጥቅማዊ ተነሳሽነት ጋር ያለው ተዛምዶ ራሱ ዝቅተኛ ተቃርኖ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህ ማለት ጥቅማጥቅማዊ ተነሳሽነት ሲጨምር የፈተና ውጤት የሚቀንስና ይህ ተዛምዶ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መኖሩን ያመለክታል ማለት ነው፡፡

## 5.3 የመፍትሔ ሃሳብ

አጥኝዋ በጥናቱ ትንታኔ ላይ በመመርኮዝ ማብራሪያና መደምደሚያን ተከትሎ የሚከተሉትንአስተያየቶች በመፍትሔ ሀሳብነት አቅርባለች፡፡

- የንባብ ተነሳሽነት ማነስ በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታና የትምህርት ውጤቶቻቸው ላይ ተጽእኖ እንደሚያሳርፍ ከጥናቱ ትንታኔ ለማየት ተችሏል፤ በመሆኑም መምህራን የተማሪዎችን የንባብ ተነሳሽነት ለማሻሻል የሚከተሉትን ሀሳቦች ተግባራዊ ቢያደርጉ ፡-
- ሁለተኛ ቋንቋ መምህራን በንባብ ትምህርት የተማሪዎችን ተነሳሽነት ለማሻሻል የንባብ ትምህርት አሰጣጥ ሂደት የተማሪዎችን ስሜት፣ ፍላጎትና ተሳትፎ በሚያነሳሳ መልኩ ቢያደርጉት፡- ለምሳሌ የሚቀርበውን የንባብ ትምህርት ርዕስ ወይም ይዘት ከተማሪዎቹ የህይወት ልምድ ጋር እያዛመዱ ቢያቀርቡ እንዲሁም የምንባቡን ርዕስ ጥቆማ በመስጠት አንብበው ወይም ተዘጋጅተው ወደክፍል እንዲመጡ ማበረታታት በመምህርና በተማሪ መካከል የሚታየው ግንኙነት ትህትናና ፈገግታን በተላበሰ አቀራራብ ቢሆን የተማሪዎችን የንባብ ተነሳሽነት የበለጠ ሊጨምር እንደሚችል ተገንዝበው መምህራን ለዚህ አቀራረብ መተግበር ቁርጠኛ ቢሆኑ ተማሪዎችን ክፍል ውስጥ በቡድንና በጥንድ ቢያደራጁ የንባብ ችሎታቸው መጠን ይጨምራል፤ ይህ ደግሞ ተማሪዎችን አነሳስቶ ለማሳተፍና ለመተጋገዝ ዕድል ስለሚፈጥርላቸው መምህራኑ በክፍል ውስጥ አቀራረብ ተማሪ ተኮር የማስተማር ስልትን ቢተገብሩ
- በመጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ደረጃ የተማሪዎች የንባብ ተነሳሽነት ካለበት ደረጃ ከፍ እንዲል ብሎም በንባብ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ሊያደርግ ስለሚችል መምህራን በመጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ደረጃ ጭምር ቢያበረታቷቸው
- የተማሪዎቹ የንባብ ተነሳሽነት ከአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት ጋር ያለው ተዛምዶ ዝቅተኛ መሆኑን በመረዳት ይህን ችግር ከግምት በማስገባት መምህራን ተማሪዎችን በማበረታታት ፍላጎታቸውን በመለየት ክትትልና ድግፍ ቢይደርጉላቸው፡፡
- የዚህን ጥናት ውጤት መነሻ በማድረግ ባሉበት ወይም በሚይስተምሩበት ትምህርት ቤት መሰል ጥናቶችን ቢያካሂዱ የተማሪዎችን የንባብ ተነሳሽነት እና የአንብቦ መረዳት ሂደት እንቅፋቶችን በጊዜ ሂደት ማስወገድ ይቻላል፡፡
- ወላጆች የልጆቻቸውን የንባብ ተነሳችነት ዝቅተኛ መሆኑን በመገንዘብ ልጆቻቸውን ሳያቋርጡ ክትትል እያደረጉ ድክመት በታየበት አስፈላጊውን ምክርና ድጋፍ ቢያደርጉ ልጆቻቸው ለንባብ በመነሳሳት ለውጤት ማብቃት ይቻላሉ፡፡

# ዋቢ መጻሕፍት


ያለዉ እንዳወቀ፡፡ (1998)የምርምርመሰረታዊመርሆችናአተገባበርባህርዳርባህርዳር ዩኒቨርሰቲ፡፡

እባቡ‹ንጉሴ፡፡(2000)፡፡ በሰቃ 2ኛ፡፡ደረጃትምህርት/ቤት የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የክፍል ዉስጥ ተሳትፎ፡፡ ጅማ ዩኒቭርሰቲ፡፡(ድ.ማ.ፅ)፡ ፡ያልታተመ፡

ስመኝ፡ አባሁና፡፡ (2002) ፡፡ በሁሩሙ ሁለተኛ ደረጃትምህርት ቤ/ትየ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያለቸዉ ተነሳሽነት፡፡ለመጀመርያ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ፅሁፍ ጅማ ዩንቨርስቲ፡፡(ያልታተመ)

ክፍሌ ሰበረዉ፡፡ (2002)፡፡ አፋቸዉን በጉሙዝኛ ቋንቋን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ ለመማር ያላቸዉ ተነሳሽነትና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዉጤት ተዛምዶ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ፅሁፍ ባህርዳር ዩኒቨርሰቲ፡፡(ያልታተመ)፡፡

ጀማል ባዲ (2001) ፡፡በሴሩ አባስ 2ኛ ደረጃትምህርትቤት የ9ኛ ክፍልተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ለመማር ያላቸዉ ተነሳሽነት ትንተና በጅማ ዩኒቨርሰቲ፡፡ያልታተመ፡፡

ዘሪቱ አስፋዉ፡፡ (2003) ፡፡በኃሞኛ ቋንቋ አፋቸዉን የፈቱ ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር ያላቸዉ ተነሳሽነት እና የዉጤት ተዛምዶ፡፡ለሁለተኛድግሪ ማሟያነት የቀረበ ፅሁፍ፡ ባህርዳር ዩኒቨርስቲ (ያልታተመ)፡፡

ተስፋዬ ኦላና ፡፡ (2014)ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው ተነሳሽነት ከውጤት ጋር ያለው ዝምድና በጅማ ዩኒቨርስቲ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

ዮሀንስ ሰለሞን ፡፡ (2013) የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ በጅማ ዩኒቨርስቲ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

Bachman (2010). Language assessemente in practice oxford university press.

Brown.H. D, (2000), principles of language learning and teaching (2nd Ed) USA.longmanInc.

Brown H.D. (1994) principles of language learning and teaching (3rd Ed) USA. Sanfarancisco state university.

Brown.HD (1997).Princples of Language learning and teaching (2ndEd) New Jersey, premire Hall

Chatterjee, S.k (2000) advanced Educational psycology, publisher.

Cole, G.P.andchan, k.s (1994) teaching princples and practes, Australiya, prentice Hall

Dorneeyei, Z. (2001) Teaching & Researching Motivation London education limited.

Elis.R. (1997) second language Acquisition oxford; oxford university press.

Elliot, J.G.etal (2005) motivation, Engagement and education performance.interbational Perspective on the contexts for learning New York: pellagara.

Freeman, D.L. and Long, M.H. (1992) An introducation to second language aequisition research (3rd edit) New York Longman group UK lit.

Gardner.R.C.(2004), Attitude motivation Test battery. International AMTB Research Project. The university of westernontario, Canada Retrieved April, 2011.

Gardner.R.C (2003) <<Attitudes, Motivation and second language learning. Ameta .Analysis of studies.

Gardner .R.c (2001) Intergrativ motivation and second language Acuquision.in z

Gardner.R.C (1985) social psycology and second language learning.therolof attitudesand motivation. London: Arnold.

Gardener R.C.(1982) language attitude and language learning in Ryan E.B(Ed),attitudesTowards Language variation:social and applied contex.Britain Edward Arnold.

Hamner,J(1991).The practice ofenglish language Teaching.londonlogmanLittle Wood,W.(1981) communicative language Teaching.cambridge:Cambridge university. Press.

Little Wood.W (1981). Communicatiive Language Teaching Cambridge: Cambirdge Univerity Paress.

Noels, K.A.etal (2003)<<Way are you learning asecondlanguage?motvational orientation Andseetdeterminatio theory>>language learning.

Norris-Holt j. (2001). Motivation as a contributing factor in second Language acquisition. Retreved April 6, 2001, Current issue. Activitites for ESL students. Things for ESL teachers. Jacqui Japan (at) Hotmail, Japan, the internet TESOL Journal.

Pintriitch, R. and Schunk. H. (2002) Motivation in Education theory, research and applications New York: Mirill prentice hall.

Scott Kissau.(n.d)gendere differences in second language motivation, An investigation of Micro.and Macro- level infuences.Refrievedapril 5,2011.

Skinner,E.C(1959)Educational psycology(4th Ed) newyork,prenties Hall, Inc.

Stern H.H(1994) fundamental concept of language Teaching.HongKong:oxford university

Stipek (1996) ,motivation and introduction in siman hand book of education USA university of California losangelus.

Ur,P.(1996) Acourse in language teaching cambridge oxford univrsty press.

Williyam, M.M, Burdan, B(1997),psycology for language teachers. Asocial constractivia approach. cambrige oxford university press.

# አባሪ ሀ የጽሁፍ መጠይቅ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲይስ ኮሌጅ

የኢትዮጲያ ቋንቋዎች እና ስነ- ጽሁፍ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል የድህር ምረቃ መርሃ ግብር

በጅማ ዞን በአጋሮ ወረዳ በጅዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በተማሪዎች የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ

ዉድ ተማሪዎች፡- የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የንባብ ተነሳሽነትና የዉጤት ተዛምዶ በሚል ርዕስ ለሚካሄድ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሁፍ በመረጃ ሰጪነት ትሳተፉ ዘንድ ተጋብዛችኂል፡፡

የመጠይቁ ዋና አላማም ከላይ ለተጠቀሰዉ የጥናት ርዕስ መረጃ ለመሰብሰብ ነዉ፡፡ በመሆኑም በሂደቱ የሚገኘዉ መረጃ ለጥናቱ ግብ መምታት ከታሰበዉ ተግባር ዉጭ የማይዉል መሆኑን አስቀድሜ እያረጋገጥኩኝ መልሶቻችሁ የእናንተን ስሜትና እምነት በትክክል የሚያንጸባርቁ እንዲሆኑ አደራዬ የጠበቀ ነዉ፡፡ ለበጎ ትብብራችሁና መልካም ተሳትፏችሁ በቅድሚያ አመሰግናለሁ ፡፡

**ክፍል አንድ፡-ዳራዊመረጃ፡- እናንተን በሚመለከት ትክክል የሆነዉን በቀረበዉ ባዶ ሳጥን ዉስጥ - ይህን ምልክት '.(√)በማድረግ አረጋግጡ፡፡**

ጾታ፡- ወንድ ------------ ሴት--------

-የክፍል ደረጃ :---------------------

የት/ቤት ስም፡-ጅዳ ---------------------- --------------------

የአፍ መፍቻ ቋንቋ አፋን ኦሮሞ----------------አማርኛ--------------------

**ክፍል ሁለት** ፡- ቀጥሎ ባለዉ ሰንጠረዥ ዉስጥ የቀረቡትን ዓ.ነገሮች ካነበብክ(ሽ) በኂላ ተሰማሚ ሆነዉ ከፊት ለፊቱ ካሉት አማራጭ መልሶች ይህንምልክት--- በማድረግ ስምምነትህን (ሽን) ግለጽ (ጪ)

መግለጫ፡- 5, በጣም እስማማለሁ 4, እስማማለሁ 3, በመጠኑ እስማማለሁ 2.አልስማማም 1 በጣም አልስማማም

| ተ ቁ | ጥያቄዎች | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አማርኛን ማንበብ በእርግጥ ያስደስተኛል | | 20 | 20 | 30 | 50 |
| 2 | ወላጆቼ ማንበብ እንድችል ሊረዱኝ ይሞክራሉ | | 20 | 10 | 20 | 60 |
| 3 | አማርኛ ማንበብ ጠቃሚ ነዉ።ምክንያቱም አማርኛን ከሚናገሩ ወገኖች ጋር በቀላሉ ለመግባባት ያስችለኛል። | | 50 | 10 | 20 | 30 |
| 4 | በአማርኛ ቋንቋ ማንበብ መቻሌ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚኖረኝን ቅቡልነት ይጨምራል | | 60 | 20 | 30 | 10 |
| 5 | አማርኛን በሁሉም ዘርፍ ለማወቅ ጠንካራ ምኞት አለኝ | | 10 | 20 | 30 | 50 |
| 6 | በአማርኛ ቋንቋ ንባብ ጊዜ ያልገቡኝን ከመምህሬ ጠይቄ መረዳት እንድችል ወላጆቼይገፋፉኛል | | 10 | 20 | 60 | 20 |
| 7 | አማርኛን ማንበብ ለእኔ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል ምክንያቱም ስነ - ጥበባቸዉንና ስነ ጽሁፋቸዉን በተሻለ ለመረዳትና ለማድነቅ ይረዳኛል፡ ፡ | | 30 | 20 | 10 | 50 |
| 8 | ወላጆቼ የአማርኛ ቋንቋ ማንበብ የሚኖረዉን ጠቀሜታ አጥብቀዉ ይነግሩኛል | | 20 | 10 | 20 | 60 |
| 9 | አማርኛን ማንበብ ጠቃሚ ነዉ ምክንያቱም ከተለያዩ ሰዎች ጋር ለመገናኘትና ለመግባባት ይረዳኛል | 10 | 50 | 10 | 20 | 20 |
| 10 | አማርኛን ማንበብጠቃሚ ነዉ ምክንያቱም ለወደፊት ሙያዬ ያስፈልገኛል | | 10 | 10 | 20 | 70 |
| 11 | ለአማርኛ ማንበብ የማዉለዉ ጊዜ ለሌሎች ትምህርቶች ከማዉለዉ ይበልጣል | 5 | 10 | 20 | 30 | 45 |
| 12 | አማርኛ የማነብበት ዋና ምክንያት ወላጆቼ/ቤተሰቦቼ አማርኛዬን እንዳሻሽል ስለሚፈልጉ ነዉ። | | 20 | 20 | 30 | 40 |
| 13 | አማርኛን ማንበብ ይጠቅማል ምክንያቱም የቋንቋዉን ተናጋሪዎች የኑሮ ስልት በቀላሉ ለመረዳት ያስችላል | | 20 | 20 | 20 | 40 |
| 14 | አማርኛን ማንበብ የሚያስፈልገዉ ጥሩ ስራ ለማግኘት ስለሚጠቅም ነዉ | | 20 | 20 | 30 | 40 |
| 15 | ዉሳኔዉ የራሴ ቢሆን አብዛኛዉን ጊዜዬን የማዉለዉ ለአማርኛ ንባብ ነዉ። | | 10 | 20 | 30 | 50 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 16 | በአማርኛ የተጻፉ ጋዜጦችን እና መጽሔቶችን ማንበብ ብችል ደስ ይለኛል | | 5 | 25 | 35 | 45 |
| 17 | አማርኛን ማንበብ ጠቃሚ ነዉ ምክንያቱም ከቋንቋዉ ተናጋሪዎች ጋር በቀላሉ ለመግባባት ያስችለኛል፡፡ | | 20 | 20 | 50 | 20 |
| 18 | አማርኛን ማንበብ ይጠቅማል ምክንያቱም አማርኛን በማንበቤ ሌሎች ሰዎች ስለሚያከብሩኝ ነዉ | | 10 | 20 | 30 | 50 |
| 19 | አማርኛ በደንብ ማንበብ እፈልጋለሁ ምክንያቱም የአማርኛ ችሎታዬን ለቤተሰቦቼ ለጓደኞቼ ለመምህሬና ለሌሎችም ለማሳየት ስለሚረዳኝ ነዉ፡፡ | | 10 | 20 | 30 | **50** |
| 20 | አማርኛን ማንበብ የሚጠቅመዉ በሌሎች ዘንድ የአዋቂነት ስም ስለሚያሰጥ ነዉ፡፡ | | 20 | 20 | 30 | 40 |
| 21 | አማርኛ ማንበብ ፍላጎት የለኝም | | 15 | 20 | 30 | 45 |
| 22 | አማርኛ ማንበብ እፈልጋለሁ | | 15 | 20 | 30 | 45 |
| 23 | አማርኛን ማንበብ የፈለግሁበት ዋና ምክንያት ፈተና ለማለፍ ነዉ፡፡ | | 20 | 20 | 30 | 40 |
| 24 | ወላጆቼ በተቻለኝ መጠን አማርኛ እንዳነብ ያበረታቱኛል፡፡ | | 10 | 20 | 20 | 60 |
| 25 | አማርኛንአቀላጥፌ ማንበብ እመኛለሁ | | 20 | 30 | 30 | 40 |
| 26 | ወላጆቼ አብዛኛዉን ጊዜዬን አማርኛ ለማንበብ ማዋል እንዳለብኝ ያምናሉ | | 10 | 10 | 20 | 70 |
| 27 | አማርኛ አነባለሁ ምክንያቱም ከቋንቋዉ ተናጋሪዎች ጋር ለመግባባት እንዲያስችለኝ ነዉ፡፡ | | 40 | 30 | 20 | 20 |
| 28 | የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ሳጠናቅቅ አማርኛ ማንበብ አቆማለሁ ምክንያቱም ፍላጎቱ የለኝም | | 30 | 20 | 20 | 40 |
| 29 | አማርኛ ማንበብ እፈልጋለሁ ምክንያቱም ወደተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ስዘዋወር ለመግባባት ይጠቅመኛል፡፡ | | 30 | 20 | 40 | 20 |
| 30 | አማርኛ ከምወዳቸዉ ትምህርቶች አንዱ ነዉ፡፡ | | 20 | 20 | 30 | 40 |
| 31 | ወላጆቼአማርኛን ማንበብ በጣም እንደሚጠቅመኝ ይገምታሉ | | 20 | 20 | 25 | 45 |
| 32 | አማርኛን ማንበብ ጊዜ መግደል ነዉ | | 20 | 25 | 35 | 30 |
| 33 | አማርኛን የማነብበት አንዱ ምክንያት ከአዳዲስ ሰዎች ጋር መገናኘትና ከክፍሌ ተማሪዎች ጋር ጓደኝነት ለመመስረት ስለሚያስችለኝ ነዉ | | 20 | 30 | 20 | 40 |
| 34 | እኔ በእርግጥ አማርኛ ለማንበብ ጠንክሬ እሰራለሁ | | 15 | 20 | 35 | 45 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 35 | በአማርኛ የንባብ ክፍለ ጊዜ የመረዳት ችግር ሲገጥመኝ ሁል ጊዜ የአማርኛ መምህሬን እገዛ እጠይቃለሁ | | 20 | 20 | 30 | 40 |
| 36 | ወላጆቼ በደንብ እንዳነብ ይመኛሉ | | 15 | 20 | 35 | 40 |
| 37 | በአማርኛ የተፃፉ መፅሄት እና ጋዜጣ ተከታትዬ አነባለሁ | | 20 | 25 | 35 | 30 |
| 38 | አማርኛ ማንበብ እፈልጋለሁ ምክንያቱም ችሎታዬን ለቤተሰቦቼ ለጓደኞቼ ማሳየት ስለምፈልግ ነው፡፡ | | 10 | 20 | 40 | 50 |
| 39 | ማንበብ የፈለኩበት ዋና ምክንያት ፈተና ለማለፍ ነው | | 20 | 20 | 30 | 40 |
| 40 | በአማርኛ ቋንቋ ንባብን ማንበብ መቻል ምኞቴ ነው፡፡ | | 30 | 20 | 40 | 20 |

## አባሪ ለ

## ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ

| | | ተከና ዉኗል | % | በከፊልተከ ናዉኗል | % | አልተከ ናወነም | % | ድም |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቁ | ከንባብ በፍት የተማሪ ድርሻ | ቁ | | ቁ | | | | |
| 1 | ሁሉም ተማሪዎች መፅሀፍ መያዝ | | | 6 | 50 | 6 | 50 | 100 |
| 2 | ስለምን እንደሚያነዉ መገመት | 1 | 8.33 | 7 | 58.33 | 4 | 33.33 | 99.93 |
| 3 | ከቀደመ እዉቀታቸዉ ጋሪ ርፅሱን ማዛመድ | | | 4 | 33.33 | 8 | 66.6 | 99.93 |
| 4 | የንባቡን አላማ መረዳት | 1 | 8.33 | 5 | 41.6 | 6 | 50 | 99.93 |
| | ለ የንባብን ጊዜ የተማርዎች ደረሻ | | | | | | | |
| 1 | ቅድመምንባብጥያቀዎች ን እያረጋገጡ መሄድ | 1 | 8.33 | 6 | 50 | 5 | 41.6 | 99.93 |
| 2 | ምንባቡን ገታ በማድረግ ጥያቀ መመለስ | | | 6 | 50 | 6 | 50 | 100 |
| 3 | የአዳድስ ቃላት ትርጉም መገመት | 2 | 16.6 | 7 | 58.33 | 3 | 25 | 99.93 |
| 4 | የምንባቡን መልፅክት ማግኘት | 2 | 16.6 | 6 | 50 | 4 | 33.33 | 99.93 |
| ሐ የድህረ ንባብ ጊዜ የተማርዎች ድርሻ | | | | | | | | |
| 1 | የምንባቡንዋና መልፅክት መናገር | 3 | 25 | 5 | 41.6 | 4 | 33.33 | 99.93 |
| 2 | ከምንባቡየወጡጥያቀዎ ችን መመለስ | 3 | 25 | 6 | 50 | 3 | 25 | 100 |

## አባሪ ሐ: የአማርኛ ፈተና

**በጅማ ዞን በአጋሮ ወረዳ በጅዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለሚካሄደዉ ጥናት የተማሪዎችን የንባብ ትምህርት ዉጤት እንደ መረጃ ለመገልገል የተዘጋጀ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ትምህርት ፈተና**

**ቀን፡-………./……../2015**

**ድርቢያብር**

አምሳያን ማፍራት ዘርን መተካት የእናት ተፈጥሯዊ ፀጋ ነው። ወላድ በድባብ ትሂድ የሚለውም ምሳሌአዊ አነጋገር ለዚህ ወደር የለሽ ክቡር ስጦታ የተሰነዘረ ሙገሳናየአክብሮት መግለጫ ነው።እናትነት የርህሄና የፅኑ ፍቅር ተምሳሌት ነው።

እናት ለልጇ ያላትን ጊዜ የማይሽረው ጠንካራ ፍቅር ለመግለፅ ሲባል ጎሽ ለልጇ ስትል ተወጋች ያባለል። ምሳሌውም በእናትና በልጅ መሀከል ያለውን ጥብቅ ትስስር ያሳያል። የዚህ ጥብቅ ግንኙነት መጠንሰሻ ስፍራ ማህፀን መሆኑ እሙን ነው።ልጅ ከእናት አብራክ የሚገኝ መሰል ፍሬ ነውና።ኢትዮጵያችን የበርካታ ብሔር ብሔረሰቦች እናት ናት።

በብሔር ብሔረሰቦች ጥላ ስር የምንገኝ ልጆቿ በሷ አምሳያ የተፈጠርን ነን። መለያችን መታወቂያችንም ኢትዮጵያዊነታችን ነው። እናት ልጆቿን እንደማታበላልጥ ሁሉ ኢትዮጵያም የማፀኗ ፍሬ የሆነውን ልጆቿን የምታየንበእኩል አይን ነው።ጉመዝ፣አኝዋክ፣ ሐድያው፣ሀረሪው፣ ሶማሌው፣ኦሮሞው፣አማራው፣ትግሬውእን ሌሎችም የአንድ እናት ልጆች ነን።

ሀገራችን ቤታችን ናት።መኖሪያ ቤት በወጉ ካልተዋቀረ ለችግር ማጋለጡ አይቀርም። የተሸነቆረ ጣራ ዝናብ ያስገባል የተነደለ ግርግዳ ለብርድ ያጋልጣል ውሽልሽል መስኮትና በርም ለዘራፊ ሲሳይ ይዳርጋል።ስለዚህ ገመና ከታቻችን ከለላ መከታችንን በጨፈቃ ሳይሆንበብትር አጥር ልንሰራ ይገባል።የብረት አጥሩ የልጆቿ የተባበረ ክንድ ነው። የአንድናት ልጆች እርስ በእርስ ተመካክረው ተስማምተው ቢሰሩ የቤታቸው ምሰሶ አይዘምም፣ጎጇቸው አይፈርስም። እንዲያውም ኢኮኖሚያቸው ዳብሮ የተመቻቸ ኑሮ ያኖራሉ።

ከእምዬ ኢትዮጵያ አብራክ የተገኘነው ኢትዮጵያውያንም በህብረት ብንሰራ ለዘመናት ከእኛ ጋር የኖረውን ድህነት አሽቀንጥረን ጥለን በስልጣኔ ጎዳና ለመራመድ እንችላለን።ስለሆነም

ለዚህ ፋታ የማይሰጥ ተልእኮ እያንዳንዳችን አቅማችን በፈቀደ መጠን ድርሻ ድርሻችንን ማበርከት አለብን ።

አንዳችን ስንደክምና ስንለፋ ሌላችን እጅና እግራችንን አጣምረን መመልከት የለብንም። ሁላችንም በየፊናችን የየበኩላችንን ድርሻ መወጣት ይጠበቅብናል።በተለይ የዚህ ሀገራዊ አደራ ተቀባይ ወጣቱ ትውልድ ነው። ለምን ብባል የአፍላ ጉልበት ባለበት፡ የዘመናዊ ዕውቀት ተቋዳሽ ነውና። ስለዝህ በወላጆቹና በአያቶቹ የድካም ማሣላይ የበቀለው ይህ አዲስ ፍሬ ጉልበቱንና ዕውቀቱን አቀናጅቶ ሀገሩይን ለማሳደግ መረባረብ ይኖርበታል ።

አንድ ታዋቂ ምሁር እንዳሉት ሀገሬ ለኔ ምን ሠራችልኝ ሳይሆን እኔ ለሀገሬ ምን ሠራሁላት? የሚለውን ጠቃሚ አባባል የዕለት ተዕለት መርሁ አንጎ ዛሬዊኑ ከዳር እስከዳር በመንቀሣቀስ አገሩን አኩርቶ እሱም ሊኮራ ይገባል ። ወጣቱ ፣ ሆ፡ ብሎ ከተነሣ ድር ቢያብር … ነውና የሚሣነው ነገር የለም ። ሁሉም በእጁ ሁሉም በደጁ ነው። እጅና ጓንት ሆኖ ለልማት ከተሠለፈ ያሰበውን ከማሳካት የሚገታው አይኖርም። ወደብልፅግና የሚወሰደውን በር ለመክፈት የሚያስችለው ቁልፋና ምስጢር ይኸው ብቻ ነው ኀብረት ።

**አንብቦ መረዳት ፈተና**

**የተፈቀደዉ ጊዜ፦ 1:15**

***መመሪያ ፩ ፡- ቀጥሎ ከተራ ቁጥር ሀ- በ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቀዎች መልስ (ሽ) 20%***

ሀ. የርህራሄና የፅኑ ፍቅር ተምሣሌት የተባለው ምንድን ነው

ለ. ኢትዮጵያ የተመሰለችው በምንድን ነው

ሐ. የእናትነት ተፈጥሮአዊ ፀጋ የተባለው ምንድን ነው

መ. ፋታ የማይሰጥ ተልዕኮ ምንድን ነው

ሠ. ሀገራዊ አደራ ተቀባዩ ዋነኛ የህብረተሰቡ ክፍል የትኛው ነው ለምን

ረ. ወደ ብልፅግና የሚወስደውን ጎዳና የሚያመቻቸው ምንድን ነው

ሰ. ወላድ በድባብ ትሂድ የሚለው ምሣሌአዊ አነጋገር ምንን ለመግለፅ የተነገረ ነው

ሽ. ጎሽ ለልጇ ስትል ተወጋች የሚለው ምሣሌአዊ አነጋገር የሚያስተላልፈው ሐሳብ ምንድን ነው

ቀ. የሦስተኛው አንቀፅ ዋና ሐሳብ ምንድን ነው

በ. የምንባቡ ዋና መልእክት ምንድን ነው

**፪. በምድብ ሀ የቀረቡትን ቃሎች በምድብ ለ ስር ከተዘረዘረው ፍቻቸው ጋር በምንባቡ መሰረት አዛምዱ ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ፀጋ | ሀ. መተጋገዝ |
| 2. ፅኑ | ለ. ተሳታፊ |
| 3. ገመና | ሐ. ማጣመር |
| 4. ተቋዳሽ | መ. ተመሣሣይ |
| 5. መረባረብ | ሠ. ስጦታ |
| 6. መርህ | ረ. ማሕፀን |
| 7. አምሳያ | ሰ. ምስጢር |
| 8. ማቀናጀት | ሸ. ጠንካራ |
| 9. አብራክ | ቀ. ምስጋና |
| 10. ሙገሣ | በ. መመሪያ |

**፫. ለሚከተሉት ቃሎችና ሐረጎች በምንባቡ ውስጥ ባላቸው አገባባችው መሠት ፍቺ ስጡ ።**

ሀ. ወደር - የለሽ

ለ. ርህራሄ

ሐ. ውሽልሽል

መ. አይዘምም

ሠ. በየፊናችን

ረ. ጊዜ የማይሽረው

ሰ. እሙና ነው

ሸ. በወጉ ካልተዋቀረ

ቀ. እጅና ጓንት

ረ. ዳር እስከዳር

**፬. የሚከተሉት ሐረጎች የሚያስተላልፉትን መልዕክት ምንባብን መሰረት አድርጋችሁ በራሳችሁ አገላለፅ ፃፉ ።**

ሀ. አምሳያን ማፍራት

ለ. የአክብሮት መግለጫ

ሐ. ጥብቅ ትስስር

መ. በእኩል ዐይን ማየት

ሠ. የተመቻቸ ኑሮ

***መመሪያ ሁለት፡- የሚከተለዉን ምንባብ በጥንቃቄ አንብበህ(ሽ) በተከታታይ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ ሃሳብ መሰረት መልስ(ሽ)፡፡30%***

***<u>ምንባብ</u>***

*ሮማን ቡና ማፍላትን ወደ ኪነታዊ ፈጠራ ከፍ ታደርገዋለች፡፡ ለሱስ አይደለም ቡና የምታፈላዉ፤ ለአምልኮትም አይመስለኝም፡፡ ለኪነታዊ ዉበቱ ስትል ይመስለኛል፡፡ እሷም ቡና በማፍላት ጥበቧ ትኮራበታለች፡፡ ቡና እናፈላለን ብለዉ ደፋ ደፋ የሚሉ ሴቶች ይገርሙኛል፡፡ ቡናን ማፍላት ረጋ ብሎ እያሳመሩ ነዉ፡፡ስነ ሥርኣቱ ዉበቱ ነዉ ደስ የሚለኝ፡፡ አለዚያ ጥቅሙ ምንድን ነዉ? ትላለች፡፡ ቡና ከማፍላቷ በፊት ተታጥባ ረጅም ያገር ልብሷን ትለብሳለች፡፡ትርክክ ብሎ የነደደ ከሰል በከሰል ምድጃ ታስቀርባለች ፡፡ልዩ የብረት ምጣዷን ከመጣዷ በፊት ለስሜቷ ተስማሚ የሆነ ሙዚቃ ትከፍታለች፡፡ ቡናዉን የምትቆላዉ ሙዚቃዉን እየተከተለች በስልት ነዉ፡፡አንድ ፍሬ ቡና አያርባትም፡፡አንድ መልክ አንድ ወዝ ይዘዉ ይወጣሉ፡፡በሙዚቃ እየታጀበችና በስልት እየተራመደች ክፍሉን ታሸተዋለች፡፡ ማሸተት ትወዳለች፡፡ መዓዛዉ ብቻ ሱስ ይቆርጣል፡፡ እንደሌሎች ሴቶች ራሷ የቆላችዉን ቡና ሌላ ሰዉ አታስወቅጥም፡፡ራሷ ናት የምትወቅጠዉ አወቃቀጡ ፍጹም መሆን አለበት ትላለች፡፡ ከሰሉ እንደገና ይራገባል እሳቱ ትርክክ ብሎ ጀበናዉን ትጥዳለች፡፡ እንግዲህ አይኖቿከጀበናዉ ላይ አይነሱም፡፡ ዉሃዉ ለተወሰነ ደቂቃ ይፈላል ቡናዉ ይጨመራል ለተወሰነ ደቂቃ ይንተከተካል ሲኒዎች በቀይ ጨርቅ በተሸፈነ ረከቦት ይቀርባሉ፡ ጀበናዉ በስነስርኣት ይወጣል እጣኑ በሥነ ሥርኣት ይጨሳል፡፡ ቡናዉ እየተንተከተከ ሲፎክር እጣኑ ቦግ ብሎ ሲጨስ የእጣኑ ሽታ እና የኣቦል ቡናዉ መኣዛ ተዋህደዉ አፍንጫ ሲያዉዱ እጆቿን እንደገና ተጣጥባ ቡናዉ እስኪሰክን ድረስ ከእጣኑ ጪስ ጋር በሃሳብ ትባክናለች ቡናዉ ይሰክናል ሀሳቧ ይሰክናል፡፡ ለዘብ ያለ ሙዚቃ ታደርጋለች ጀበናዉን ከፍ አድርጋ ቡናዉን በረጅሙ በቀስታ በቀጭኑ ትቀዳለች፡፡ የምታፈላዉ ቡና እኮ እንዲያዉ ቡና አይደለም፡፡ አንዱ ብቻ ይበቃል እሷም ብትሆን የምታፈላዉ ቡና ከሶስት ሲኒ አይበልጥም፡፡ እጣኑ ቦግ ሲል በአይነ ህሊናዬ ታየኝ እሷም በእጣኑ ጢስ ዉስጥ ፡፡የቡናዉ መዓዛ መጣብኝ ፡፡ ፊት ለፊት ካልተቀመጥኩኝ እሺ ብላ ቡና አታፈላም፡፡*

ከኦሮማይ *መጽኃፍ ገጽ* 264-265 *የተወሰደ*

---------11. *ሮማን ቡና የምታፈላዉ------ ሀ. ለሱስ ለ. ለምልክት ሐ. ለደንቡ*

*መ. ለኀረቤት ስትል*

--------12. *ለስሜቷ ተስማሚ -----ለሚለዉ ሀረግ ተመሳሳዩ*

*ሀ.ለዝግጅቱ የሚስማማ ለ. ለፍላጎቷ ተስማሚ ሐ. ለሱሷ ተስማሚ መ. ሁሉም መልስ ነዉ*

--------13. አወቃቀጡ ፍጹም መሆን አለበት ሲል---- ሀ.አወቃቀጡ የተለየ ነዉ

ለ.አወቃቀጡ አንድአይነት ነዉ ሐ. አወቃቀጡ በጣም የደቀቀ ነዉ

መ.ሁሉም መልስ ነዉ

--------14. አፍንጫን ያዉዳል ሲል ሀ.አፍንጫን ይሰነፍጣል ለ.አፍንጫን ያስነጥሳል

ሐ. ሀ እና ለ መ. ለአፍንጫ ጥሩ ሽታ አለዉ

-------15. ከእጣኑ ጋር በሃሳብ ትባክናለች ሲል ---

ሀ. ባሃሳብ ትዋልላለች ለ. ባሃሳብ ትብክነከናለች ሐ.ባሃሳብ ትጔዛለች መ.ሁሉም መልስ ነዉ

-------16. ሃሳቧ ይስክናል ሲል------------

ሀ. ሃሳቧ ይበርዳል ለ. ሃሳቧ ይቀዘቅዛል ሐ. ሃሳቧ ይረጋል መ. ሀ እና ለ

--------17. ለዘብ ያለ ሙዚቃ ሲል ----ሀ. ለስለስ ያለ ለ. ሞቅ ያለ ሐ. ፈዘዝ ያለ

መ. የሚያሳዝን

--------18. ቡና እናፈላለን ብለዉ ደፋ ደፋ የሚሉ ሴቶች ይገርሙኛል። የተሰመረበት ቃል

ሀ. ጣደፍ ጣደፍ ለ. ጎንበስ ቀና ሐ. ረጋ የሚሉ መ. ሀ እና ለ

-------19. ቡናዉን የምትቆላዉ ሙዚቃዉን እየተከተለች በስልትነዉ። የተሰመረበት ቃል--

ሀ. በእርጋታ ለ. በችኮላ ሐ. በዘዴ መ. በዉዝዋዜ

--------20. የእጣኑ ሽታ እና የአቦል ቡናዉ መአዛዉ ተዋህደዉ ሲል የተሰመረበት ቃል ተቃራኒዉ

ሀ. ተጣምረዉ ለ. ተለያይተዉ ሐ. ተላልፈዉ መ. ተጣልተዉ

**አባሪ መ**

**APPENDIX –ENGLISH VERSION**

1. I really enjoy learning English.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

2. My parents try to help me to learn English.

Strongly Disagree Moderately Disagree Slightly Disagree Moderately Agree Strongly Agree

3. Studying English is important because it will allow me to be more at ease with people who speak English.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

4. Being able to speak this language will add to my social status.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

5. I have a strong desire to know all aspects of English.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

6. My parents urgue me to seek help for my teacher if I am having problems with my English.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

7. Studying English can be important for me because it will enable me to better understand and appreciate their art and literature.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

8. I am learning this language to understand films, videos or music.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

9. My parents have stressed the importance English will have.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

10. Studying English is important because it will allow me to meet and converse with moree and varied people.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

11. Studying English is important because I will need it for my career.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

12. I would rather spend more time in my English class and less in other classes.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

13. The main reason I am taking this class is that my parents / my spouse/ my supervisors/ want me to improve my English.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

14. Studying English can be important for me because it will enable me to better understand the English way of life.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

15. Studying English is important because it will be useful in getting a good job.

16. If it were up to me, I would spend all of my time learning English.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

17. I wish I could read newspapers and magazines in many foreign languages.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

18. Studying English can be important for me because I will be able to interact more easily with speakers of English.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

19. Studying English is important because other people will respect me more if I know English.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

20. I don't bother checking my assignments when I get them back from English teacher.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

21. I want to do well in this class because it is important to show my ability to my family /friends/supervisors/others.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

22. Studying English is important because it will make me more educated.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

23. I really have no interest in foreign languages.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

24. My parents are very interested in everything I do in my English class.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

25. The main reason I need English is to pass examination.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

26. I love learning English.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

27. My parents encourage me to practice me English as much as possible.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

28. I wish I were fluent in English.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

29. My parents think I should devote more time to study English.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

30. I would rather see a TV program dubbed into our language than in its

31. own language with studies.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree

Moderately Agree Strongly Agree

32. I am learning English because i want to spend a period of time in an English-speaking country

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

33. When I leave school, I will give up the study of English because I am not interested in it.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

34. I want to learn English because it is useful when travelling in many countries.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

35. English is one of my favorite courses

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

36. My parents feel that i should continue studying English all through school.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

37. I enjoy the activities of English class much more than those of my other classes.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

38. My parents feel that it is very important for me to learn English.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

39. Learning English is a waste of time.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

40. One reason i learn English is that i can meet new people and make friends in my English classes.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

41. I really work hard to learn English.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

42. When i have problem in understanding something in my English class I always ask my teacher for help.

Strongly disagree Moderately disagree Slightly disagree Moderately Agree Strongly Agree

## የአጥኚው ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜ የተጠቀሰው አጥኚ ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ የግል ስራዎቼ መሆናቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለው፡፡ አለማቀፋዊ ተቀባይነት እንዳላቸው ልምዶች መሰረት በጥናቴ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን መሳሪያዎችና ስራዎች በሙሉ በዋቢ መጽሀፍት ስር በማስቀመጥ ዋጋ ሰጥቼባቸዋለሁ፡፡

የአጥኚው ሰም -----------------

ፊርማ -------------------------